# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 088 ኅዳር 28 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ምክክሩ ኢትዮጵያና አውሮፓ ኅብረት

## ግንኙነታቸውን በአዲስ መልክ ለማጠናከር ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳያል

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የአውሮፓ ኅብረት ልዑካን ጋር የተደረገው ውይይት ኢትዮጵያና አውሮፓ ኅብረት ግንኙነታቸውን በአዲስ መልክ ለማጠናከር ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳያል ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን አስታወቁ፡፡

ኢትዮጵያና የአውሮፓ ኅብረት ግንኙነታቸውን ማደስ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ምክክር አካሂደዋል፡፡ ምክክሩ እ.ኤ.አ በ2016 በኢትዮጵያና በአውሮፓ ኅብረት መካከል በተፈረመው የስትራቴጂካዊ ተሳትፎ ስምምነት መሠረት በየዓመቱ የሚካሄድ ነው፡፡

ምክክሩን የመሩት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን እንደገለጹት፤ በየዓመቱ የሚካሄደው ውይይት የኢትዮጵያ መንግሥት እና የአውሮፓኅብረት አባል ሀገራቱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር ያላቸውን ቁርጠኝነት ያሳያል፡፡

ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ኅብረት ጋር ያላትን ግንኙነት ለማጠናከር ቁርጠኛ ናት ያሉት አቶ ደመቀ፤ የስትራቴጂክ አጋር ለመሆን የተፈራረሙትን ስምምነት በትክክለኛው መንገድ እየሄደ ለመሆኑ ማሳያ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ምክክሩ ኢትዮጵያና ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ !

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia


## "አዲስ አበባ ከተማ የስማርት አገልግሎቶች ተምሳሌት እንድትሆን ሥራዎች እየተሠሩ ነው"

-ከንቲባ አዳነች አቤቤ

ገጽ 6

## "አዲስ አበባን የሁከትና የብጥብጥ ማዕከል ለማድረግ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ቡድኖች ሴራ ከሸፈ"

- የጸጥታና የደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በሰላማዊ ሰልፍ ሽፋን አዲስ አበባን የሁከትና የብጥብጥ ማዕከል ለማድረግ የሽብር ተልዕኮ ተቀብለው በህቡዕ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ ቡድኖች ሴራ መክሸፋን የጸጥታና የደኅንነት የጋራ ግብረ- ኃይል አስታወቀ፡፡

የጸጥታና የደኅንነት የጋራ ግብረ- ኃይል ለኢፕድ በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ፅንፈኛ ኃይሎችና የሽብር ቡድኖች በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች አንዳንድ አካባቢዎች በትጥቅ የታገዘ ግፍና ግድያ በመፈፀም እንዲሁም የጸጥታ ችግሮችን በመፍጠር የኅብረተሰቡን ሰላማዊ እንቅስቃሴ እያወኩ ይገኛሉ፡፡

እነዚህ ፅንፈኛ ኃይሎች እና የሽብር ቡድኖች በአማራና ኦሮሚያ ክልሎች በአንዳንድ አካባቢዎች እየፈፀሙት ያለውን ፀረ- ሰላም እንቅስቃሴ የኢትዮጵያ እና የአፍሪካ መዲና እንዲሁም የዓለም-አቀፍ ተቋማት መቀመጫ ወደ ሆነችው አዲስ አበባም በማስፋፋት በሚፈጠረው ሁከትና ብጥብጥ ሀገሪቱን የትርምስ

"አዲስ አበባን የሁከትና... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## "በለውጡ ማግስት በተሠሩ ሥራዎች ክልሉ በልዩ ድባብ የብሔር ብሔረሰቦች በዓልን እያከበረ ይገኛል"

-አቶ ሙስጠፌ መሐመድ
የሱማሌ ክልል ርእሰ መስተዳድር

**ዘሳለም ግዛው**

ጅግጅጋ፡- በለውጡ ማግስት በተሰሩ ሥራዎች ክልሉ በልዩ ድባብ የብሔር ብሔረሰቦች በዓልን እያከበረ ይገኛል ሲሉ የሱማሌ ክልል ርእሰ መስተዳድር አቶ ሙስጠፌ መሐመድ ተናገሩ፡፡

የዘንድሮውን 18ኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን "ብዝሃነትና እኩልነት ለሀገራዊ አንድነት" በሚል በጅግጅጋ ከተማ በተለያዩ መርሀ ግብሮች እየተከበረ ይገኛል።

ርእሰ መስተዳድሩ አቶ ሙስጠፌ በዓሉን አስመልክተው ባስተላለፉት መልእክት፣ በለውጡ ማግስት በተሠሩ ሥራዎች ክልሉ በልዩ ድባብ የብሔር ብሔረሰቦች በዓልን እያከበረ ይገኛል ብለዋል፡፡

ባለፉት አምስት ዓመታት ለውጡን ተከትሎ በሱማሌ ክልል በተሠሩ የልማት፣ የማኅበራዊ እና የፖለቲካ ሥራዎች የሱማሌ ክልል ፀጥታ የተረጋጋ ሁኔታ ውስጥ እንዲገኝ ማስቻሉን የጠቀሱት የክልሉ ርእሰ መስተዳድሩ፤ በዓሉ በሱማሌ ክልል መከበሩ በቀጣይ የተለያዩ ሀገራዊ መርሀ ግብሮችን ለማስተናገድ አቅም የተፈጠረበት፣ ተሞክሮም የተገኘበት መሆኑን አመልክተዋል።

የክልሉ ነዋሪዎች እንግዶችን ተቀብለው እያስተናገዱ እንደሚገኙ በመጠቆምም፣ የበዓሉ ታዳሚዎች የሱማሌ ክልል ሕዝብን እንግዳ ተቀባይነት እና ፍቅር




እንደሚመሰክሩ እናምናለንም ብለዋል።

በዓሉ በክልሉ ለሁለተኛ ጊዜ መከበሩን ያስታወሱት ርእሰ መስተዳድሩ አቶ ሙስጠፌ 8ኛው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ሲከበር ክልሉ በከፍተኛ የጸጥታ ችግር ውስጥ እንደነበር ጠቁመዋል።

ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት በሚፈፀምበትና

"በለውጡ ማግስት በተሠሩ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል









ደሳለኝ ጴጥሮስ (ዶ/ር)

# ብቁ አመራርና ባለሙያ ለማፍራት የስልጠና ጥራትን ማሳደግ ይገባል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በከተማዋ ብቁ አመራርና ባለሙያ ለማፍራት የሚሰጡ ስልጠናዎችን ተደራሽነትና ጥራት ማሳደግ እንደሚገባ የአዲስ አበባ ከተማ አመራር አካዳሚ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ከባለድርሻ አካላት ጋር የምክክር መድረክ በትናንትናው እለት አካሂዷል፡፡

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ፕሬዚዳንት ደሳለኝ ጴጥሮስ (ዶ/ር) በመድረኩ ላይ እንደገለፁት፤ አካዳሚው ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አመራርና ባለሙያዎች ስልጠና እየሰጠ ይገኛል፡፡

ስልጠናውን የወሰዱ አመራርና ባለሙያዎች በአገልግሎትና በአመራር አሰጣጥ ለውጥ ቢያሳዩም የከተማው ነዋሪ አሁንም የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ያነሳል ያሉት ኃላፊው፤ እነዚህ ጥያቄዎችን ለመመለስና ብቁ አመራሮችና ባለሙያዎችን ለማፍራት የስልጠና ተደራሽነትና ጥራትን ማሳደግ ይገባል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ደሳለኝ (ዶ/ር) ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2015 ዓ.ም ከ47 ሺህ በላይ የሚሆኑ አመራሮችንና ባለሙያዎችን በአጭርና በረጅም ጊዜ ማሰልጠኑን አውስተው፤ በቀጣይ ተደራሽነቱን በማስፋት በርካታ ባለሙያዎች ለማሰልጠን እንደሚሰራ አስታውቀዋል፡፡

ስልጠናዎችን ተደራሽ ለማድረግ ሰልጣኝን ማዘጋጀት ጀምሮ እስከ ስልጠናው ውጤታማነት ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር መስራት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በአካዳሚው የሚሰጠው በጥናት ላይ የተመሠረቱ ስልጠናዎች የከተማዋን ዘመናዊነትና እድገት የሚመጥን አመራር እና ባለሙያ ለመፍጠር ያስችላል ያሉት ደሳለኝ (ዶ/ር)፤ የአመራሩንና የባለሙያውን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም በመገንባት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋለውን የመልካም አስተዳደር ችግር ለመፍታት ይረዳል ብለዋል፡፡

አካዳሚው የአጭር፣ መካከለኛና ረጅም ጊዜ ስልጠናዎች በመስጠት የተቋማትን የአፈፃፀም አቅምን ለማሳደግ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አካዳሚው በከተማ አስተዳደሩ ተቋማትን ለማዘመን እየተተገበሩ ያሉ የቴክኖሎጂ ሥራዎች ላይ ችግር ፈቺ ምርምሮችን በመሥራት ዘመናዊ ከተማን ለመገንባት ለተያዘው ግብ የድርሻውን እያበረከተ መሆኑንም ዶክተር ደሳለኝ አስታውቀዋል፡፡

በ2006 ዓ.ም የተመሰረተው አካዳሚው ለአመራሩ እና ለባለሙያው ከሚሰጠው ስልጠና በተጨማሪም ችግር ፈቺ የጥናትና የማማከር ሥራዎችን ከባለድርሻ አካላት ጋር በመተባበር ውጤታማ ሥራ እየሠራ መሆኑን አመልክተው፤ ከምክክር መድረኩም ገንቢ ሃሳብ እና ግብአቶችን በማግኘት ለቀጣይም የላቀ አፈጻጸም ለማስመዝገብ እንደሚሠራም ጠቁመዋል፡፡

# ለሦስት ቀናት የሚቆይ ዓለም አቀፍ የእርሻ እና የምግብ ንግድ ትርኢት ተከፈተ

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የተዘጋጀ ለሦስት ተከታታይ ቀናት የሚቆይ 14ኛው ዓለም አቀፍ የእርሻ እና የምግብ ንግድ ትርዒት በአዲስ አበባ ሚሊኒየም አዳራሽ ተከፍቷል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የንግድና ግብይት ዘርፍ ምክትል ኃላፊ አቶ መስፍን አሰፋ በመርሀ ግብሩ ለጋዜጠኞች በሰጡት ማብራሪያ፤ የንግድ ትርዒቱ የተለያዩ አምራቾች እንዲሁም ኢንዱስትሪዎች የገበያ ትስስር እንዲያገኙና የቴክኖሎጂ ልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ትልቅ እድል የሚፈጥር ነው ብለዋል፡፡




የንግድ ትርኢቱ የተለያዩ ዓለም አቀፍ አምራች ኩባንያዎች የሚሳተፉበት በመሆኑ ሌላው ዓለም በቴክኖሎጂና በእውቀት የደረሰበትን ደረጃ ለማወቅ ዕድል ይፈጥራል ያሉት ኃላፊው፤ የሀገር ውስጥ አምራች ኢንዱስትሪዎችና አምራች አርሶ አደሮች ምርቶችን በላቀ ደረጃ ማምረት የሚችሉበትን የልምድ ልውውጥ የሚያገኙበት እንደሆነም ጠቅሰዋል፡፡

የንግድ ትርኢቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለተጀመሩ የሌማት ትሩፋት ፕሮጀክት ውጤታማነትም የላቀ ሚና ይኖረዋል ያሉት ኃላፊው፤ የከተማ ግብርናን ለማስፋፋት በከተማ አስተዳደሩ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችን ይበልጥ በማጠናከር ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ እየተደረገ ላለው ጥረት ስኬትም በጎ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወ/ሮ መሰንበት ሸንቁጤ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ግብርና ላይ የተመረኮዘ እንደመሆኑ በግብርናው መስክ የተሰማራውን የግሉን ዘርፍ ማጠናከር ይገባል ብለዋል፡፡

በተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች ግብርናውን በማዘመንና የግብርና ውጤቶችን ምርታማነት በመጨመር ሀገሪቱ በዘርፉ ያላትን አቅም ማሳደግና ከዘርፉም መጠቀም እንደሚገባ አብራርተዋል፡፡

የኢንዱስትሪው ዘርፍ በኢኮኖሚው መስክ ያለውን አነስተኛ ሚና መጨመርና ግብርናውን በኢንዱስትሪ ማላቅ እንደሚገባም ፕሬዚዳንቷ አሳስበዋል፡፡

መሰል ዓለም አቀፍ የንግድ ትርኢቶች በአምራቾች፣ በኢንዱስትሪዎችና በንግዱ ማኅበረሰብ መካከል ትስስር ለመፍጠርና ለዓለም አቀፍ አምራቾች የኢንቨስትመንት አማራጮችን በማመላከት ረገድ የሚኖረው አስተዋጽኦ ሰፊ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

“Maximizing Value Additions through Agro Business“ በሚል መሪ ቃል እየተካሄደ በሚገኘው የንግድ ትርኢት ከኬንያ፣ ሞሮኮ፣ የተባበሩት አረብ ኢምሬቶች፣ ቱርክ፣ ኮሶቮ፣ ሞሪሺየስ እና ሕንድ የመጡ ኩባንያዎችና በርካታ የሀገር ውስጥ አርሶ አደሮችና አምራች ኢንዱስትሪዎች እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡

# ጽዳትና ውበት የአዲስ አበባ ቋሚ መለያ እንዲሆኑ የተጀመረው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ይቀጥላል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- ጽዳትና ውበት የአዲስ አበባ ከተማ ቋሚ መለያ እንዲሆኑ የተጀመረው ከተማዋን ጽዱ የማድረግ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል የአዲስ አበባ ከተማ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ገለጸ፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የበጋ ወራት የፅዳት ንቅናቄ ማስጀመሪያ መርሀ ግብር የአስተዳደሩ አመራሮች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ የትምህርት ማኅበረሰብ፣ የኪነጥበብ ባለሙያዎች፣ የጽዳት አምባሳደሮች፣ የስፖርት ማኅበረሰብና የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተገኙበት ትናንት አካሂዷል፡፡

በመርሀ ግብሩ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይዘሮ ሂከማ ከይረዲን እንደገለጹት፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ቆሻሻ ብክለት የሚያስከትል መሆኑ ቀርቶ ገቢ ማግኛ ሀብት ማድረግ ተችሏል፡፡

ቆሻሻን መልሶ በመጠቀም ሂደት ለበርካቶች የሥራ ዕድል መፈጠሩን የገለጹት ሥራ አስኪያጇ፣ ከእነዚህም ውስጥ አብዛኛዎቹ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን ከመደገፍ አልፈው ወደ ባለሀብትነት ተሸጋግረዋል ሲሉ ገልጸዋል።

ይህንን መልካም ተሞክሮ ለማስቀጠልም ሁሉም ባለድርሻ አካላት ኃላፊነቱን ሊወጣ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።

ወይዘሮ ሂከማ ጽዳት የአዲስ አበባ መለያና ቋሚ የኅብረተሰብ ባህል ሆኖ እንዲቀጥል ለማስቻል በመስኩ የተመዘገቡ ሥራዎች ተጠናክረው እንደሚቀጥሉ አመልክተዋል፡፡

ከዚህ ቀደም ከተማዋን የማጽዳት ሥራ ዓለም አቀፍ እውቅና አስገኝቷል ያሉት ሥራ አስኪያጇ፤ በከተማ ፅዳት ዘርፍ እስካሁን የተመዘገቡ ውጤቶችን በማጠናከርና መልካም ተሞክሮዎችን በማስፋት ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሠራ አብራርተዋል፡፡

አዲስ አበባን በዓለምአቀፍ ደረጃ ለኑሮና ለሥራ ተመራጭ ለማድረግ የተያዘው እቅድ እንዲሰምር አዳዲስና ዘመናዊ አሠራሮችን ከመዘርጋት ተጨማሪ ሁሉም የማኅበረሰብ ክፍል በበጋው የጽዳት ንቅናቄ መርሀ ግብር ላይ በንቃት እንዲሳተፍ ወይዘሮ ሂከማ ጥሪ አቅርበዋል፡፡



የአዲስ አበባ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር እሸቱ ለማ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ አዲስ አበባን ጽዱና ውብ ከተማ ለማድረግ ባለቤት ሊሆን የሚገባው ማኅበረሰቡ ነው ብለዋል።

በከተማዋ ነዋሪዎች ዘንድ የቆሻሻ አወጋገድና በተለይም የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ላይ በርካታ መሻሻሎች መኖራቸውን የገለጹት ሥራ አስኪያጁ፤ ቆሻሻን ወደ ሀብትነት ለመቀየር በሚደረገው ጥረት የውጭ ምንዛሬን ጭምር የማምጣት አቅም እየተፈጠረ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በየሳምንቱ ዓርብ ከጠዋቱ 1:30 እስከ 2:30 ሰዓት ድረስ ተቋማት ግቢያቸውን እና ከግቢያቸው 50 ሜትር ርቀት ሠራተኞቻቸውን በማስተባበር ማጽዳት እና ቅዳሜ ደግሞ በሁሉም የመኖሪያ ብሎኮች የሚገኙ ነዋሪዎች ከጠዋቱ 12:00-2:00 ሰዓት ድረስ አካባቢያቸውን በማጽዳት የበጋው የጽዳት መርሀ ግብር አካል መሆን እንዳለባቸው እሸቱ (ዶ/ር) አስታውቀዋል፡፡



## “የሸዋል ኢድ የዓለም ቅርስ ሆኖ መመዝገቡ የቱሪስት ፍሰት እንዲጨምር ያደርጋል”

**- ወይዘሪት ሌንሳ መኮንን የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ**

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የሸዋል ኢድ የዓለም ቅርስ ሆኖ መመዝገብ የቱሪስት ፍሰቱ እንዲጨምር እንደሚያደርግና የሀገር መልካም ገፅታ ግንባታ ላይ የራሱ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው ቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ።

የቱሪዝም ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሪት ሌንሳ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የሀረሪ ሕዝብ ባህላዊ በዓል ሸዋል ኢድ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ተቋም (ዩኔስኮ) በማይዳሰስ ቅርስነት መመዝገቡ የቱሪስት ፍሰቱ እንዲጨምር ያግዛል።

በተጨማሪም የሀገር መልካም ገፅታ በመገንባት ረገድ ፋይዳው የላቀ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በተለይም የክልሉን የቱሪዝም ማዕከልነት በማሳደግ የሕዝብን ተጠቃሚነት ያሳድጋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ቅርሶች በዓለም ቅርስነት ሲመዘገቡ በሀገር ውስጥ ያሉ ቅርሶችን ምንነት ለማወቅ እንደሚረዳ አብራርተዋል።

ይህም የሀገር ገጽታን ለመገንባት ትልቅ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

የሸዋል ኢድ በሐረሪ ብሔር ብሔረሰቦች ዘንድ የሚከበር ዓመታዊ የሶስት ቀን በዓል መሆኑን ጠቅሰው፤ በዓሉ በሐረሪ ሕዝብ ዘንድ በተለያዩ መቅደሶች በጀጎል መግቢያ በር ይከበራል ብለዋል።

በዓሉ ለቀጣዩ ትውልድ በረከት የሚሰጥበት መድረክ ሆኖ የሚያገለግል መሆኑን አስገንዝበው፤ በተለይም ለወጣቶች ባህላዊ እሴቶችን፣ ወጎች ለመማር እንደሚረዳ ገልጸዋል።

ሹዋሊድ የኪነጥበብ፣ የአፍ ወጎች፣ የባህላዊ አልባሳትና ሌሎች የባህል ክፍሎች የሚተላለፉበት መድረክ ነው ያሉት ወይዘሪት ሌንሳ፤ ማህበራዊ ትስስርንና የማንነት ስሜትን ያበረታታል ብለዋል።

በዓሉ የባህል ልውውጥ የሚደረግበት፣ የእጅ ሙያ ውጤቶች የሚታዩበት ልዩ በዓል መሆኑን ገልጸው፤ ኢትዮጵያ ካሏት ደማቅ ማኅበራዊ እሴቶች አንዱ የሸዋል ኢድ በዓል አከባበር መሆኑን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የቱሪዝም ሀብቶቿን ባስተዋወቀች ቁጥር ዓለም ስለ ኢትዮጵያ ትልቅነት ይበልጥ እንዲያውቅ እንደሚረዳ የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜያት ውስጥ ብቻ በርካታ ቅርሶችን ማስመዝገቧን አንስተዋል።

የባሌ ተራሮች ብሔራዊ ፓርክና የጌዲኦ መልካ ምድርን በሚዳሰስ ቅርስነት እንዲሁም አሁን ላይ የሸዋል ኢድን በማይዳሰስ ቅርስነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ማስመዝገቧም ዓለም ስለ ኢትዮጵያ ትልቅነት ይበልጥ እንዲያውቅ ያስችለዋል ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ወይዘሪት ሌንሳ ገለጻ፤ የቱሪዝም ሀብቶችን ማስተዋወቅ ሲቻል የውጭ ዜጎች ኢትዮጵያ የበርካታ ቅርስ ባለቤት መሆኗን ይገነዘባሉ።ይህም በቱሪዝም ዘርፉ ላይ የራሱ የሆነ በጎ ተፅዕኖ ይፈጥራል።

የቅርስ ጥበቃ ባለስልጣን፣ የሀረሪ ክልል የባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ የሸዋል ኢድ በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገብ ላደረጉ አካላት ሚኒስትር ዴኤታዋ ምስጋና አቅርበዋል።

የሸዋል ኢድ በዓል በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ተቋም (ዩኔስኮ) በማይዳሰስ ቅርስነት የተመዘገበ ሲሆን፤ ይህም ኢትዮጵያ በማይዳሰስ ቅርስነት ካስመዘገበቻቸው 5ኛ ቅርስ ሆኗል።

# ለመከላከያ ሠራዊት ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ የሚያወጡ የሕክምና ቁሳቁሶች ድጋፍ ተደረገ

**ማርቆስ በላይ**



አዲስ አበባ፡- ብሔራዊ ጀግኖችና ሕፃናት አምባ ከዓለም አቀፍ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ያገኘውን ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ግምት ያላቸውን የተለያዩ የሕክምና ቁሳቁሶች ለሀገር መከላከያ ሠራዊት ድጋፍ አስረከበ፡፡

በድጋፍ ርክክቡ ወቅት የብሔራዊ ጀግኖችና ሕፃናት አምባ ምክትል ቦርድ ሰብሳቢ ሻለቃ ተስፋዬ ወንድሙ፤ ለሀገር መከላከያ ሠራዊት የተበረከቱ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ግምት ያላቸው የሕክምና ቁሳቁሶች ከተለያዩ ዓለም አቀፍ በጎ አድራጎት ድርጅቶች የተገኙ ናቸው ብለዋል።

ድጋፉ የሀገርን ሰላም ለማጽናት ህይወቱን እየሰጠ ለሚገኘው መከላከያ ሠራዊት አባላት የሚውል ነው ያሉት ሻለቃ ተስፋዬ፤ የኢትዮጵያ ጀግኖችና ሕፃናት አምባ ማኅበር ድጋፍ ሲያቀርብ ደስታ ይሰማዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ድጋፉ ከአንድ ቢሊዮን ብር በላይ ግምት ያላቸው የተለያዩ የሕክምና ቁሳቁሶችን ያካተተ መሆኑን ጠቁመው፤ ዊልቸር፣ ዳይፐር፣ የሕክምና ስሪንጅ፣ የእጅ ጓንቶችን ጨምሮ የተለያዩ የሕክምና ቁሳቁሶችን ያካተተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ሻለቃ ተስፋዬ አክለውም፤ ማኅበሩ ለሀገር መከላከያ ሠራዊት የሚያደርጋቸውን ድጋፎች አጠናክሮ እንደሚቀጥል አመላክተዋል፡፡

የመከላከያ ጤና ዋና መምሪያ ኃላፊ ሌተናል ጄነራል ጥጋቡ ይልማ ድጋፉን በተረከቡበት ወቅት እንደተናገሩት፤ የተገኘው የሕክምና ቁሳቁስ ድጋፍ የጤና መምሪያው አገልግሎት ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚረዳ ነው፡፡

ድጋፉ ተቋሙ እያደረገ ላለው ጥረት የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ያስችላል ያሉት ሌተናል ጄነራሉ፤ ጀግኖችና ሕፃናት አምባ ማኅበር በሕክምና ቁሳቁስ፣ በመድኃኒትና በሌሎች አላቂ ቁሳቁሶች ከፍተኛ ድጋፍ በማድረግ ላይ በመሆኑ ሊመሰገን ይገባዋል ብለዋል፡፡

ድጋፉ አራት ነጥብ አራት ቶን ዳይፐር፣ 40 ዊልቸሮች ፣ 20 ድጋፍ ሰጪ መራመጃዎች፣ የሕክምና ጓንቶችን ጨምሮ የተለያዩ የሕክምና ቁሳቁሶችን እንደሚያካትት አስረድተዋል፡፡

ማህበሩ በተለያዩ ጊዜያት ለሠራዊቱ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ላይ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዚህ ቀደም ከ600 በላይ የሕክምና የመኝታ አልጋዎች እንዲሁም የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መገልገያ ዕቃዎችን ድጋፍ በማድረግ አስተዋጽኦ ማበርከቱን አስታውሰዋል።

ድጋፉ በሀገር ውስጥ ለሚገኙ የሀገር መከላከያ ሠራዊት ሆስፒታሎች የሚሰራጭ መሆኑም ተገልጿል፡፡

# የኅብረት ሥራ ማኅበራት የራሳቸውን ባንክ እንዲያቋቁሙ እየተሠራ ነው

## -ማኅበራቱ ከ50 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል አስመዝግበዋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የኅብረት ሥራ ማኅበራት የራሳቸው ባንክ እንዲያቋቁሙ አቅዶ እየሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን አስታወቀ፡፡ ማኅበራቱ ከ50 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘገቡ ሲሆን፤ በዓመት በአማካኝ 15 ቢሊዮን ብር ብድር እንደሚሰጡ ተመላክቷል፡፡

የቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ75ኛ በኢትዮጵያ ለሁለተኛ ጊዜ "በቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማኅበራት አባላት እርስ በእርስ ይደጋገፋሉ" በሚል መሪ ሃሳብ ትናንት ተከብሯል፡፡

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር ጌታቸው መለሰ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የፋይናንስ አቅማቸውንና የአባላት ፍላጎት ተደራሽነትን ከማስፋፋት ባሻገር የራሳቸው ባንክ እንዲያቋቁሙ የተለያዩ ሥራዎችን ለመሥራት ታቅዷል።

የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት በተለይም የመደበኛ ባንክ አገልግሎት ተደራሽነት ለሌላቸው በገጠር እና ከተማ ለሚኖሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የአኗኗር ባሕላቸውን መሠረት ያደረጉ የቁጠባ፣ የብድርና አነስተኛ የኢንሹራንስ አገልግሎቶች እያቀረቡ መሆኑን ጠቁመዋል።

አገልግሎታቸውን በማሳደግ ራሱን የቻለ ባንክ እንዲያቋቁሙ የሚረዳ አሠራር ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ጌታቸው፤ የፋይናንስ አቅማቸውን በማሳደግ ባንክ እንዲያቋቁሙ ማድረግ ውጤታማነታቸውን ያጎለብተዋል ብለዋል።

የማኅበራቱን የፋይናንስ አገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመንና አቅማቸውን ያገናዘበ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመዘርጋት ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲሰጡ የሚያስችል አቅም ለመገንባት በትኩረት ይሠራል ሲሉ ተናግረዋል።

በከተማ ደረጃ የነበረው የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት አደረጃጀትን በገጠርም ማስፋፋት በመቻሉ በርካታ ውጤቶችን ማስመዝገብ እንደተቻለ ገልጸዋል፡፡

በገጠር ቀበሌዎችና በከተሞች ደረጃ ከ23 ሺህ በላይ መሠረታዊ የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማኅበራት እና 128 ዩኒየኖችን በማደራጀት የፋይናንስ አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን አስታውቀዋል።

በእነዚህ ማኅበራትም ከስምንት ሚሊዮን በላይ አባላት መኖራቸውን ተናግረዋል፡፡

ተቋማቱ የቁጠባ ባህልን በማሳደግ ከ50 ቢሊዮን ብር በላይ ቁጠባና ዕጣ ያሰባሰቡ ሲሆን፤ በዓመት በአማካይ ከ15 ቢሊዮን ብር በላይ ብድር በማቅረብ አንድ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን የኅብረት ሥራ አባላት ተጠቃሚ እንደሚያደርጉ አመላክተዋል፡፡

ለአርሶና አርብቶ አደር ለምርትና ምርታማነት ዕድገት ወሳኝ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ያለባቸውን የፋይናንስ ማነቆ ለመቅረፍ ማኅበራቱ ጠቀሜታ እንዳላቸው አስገንዝበዋል፡፡

በተመሳሳይ በከተማ ለሚኖሩ ዜጎች የመኖሪያ ቤት ችግሮችንና ለቤት ግንባታና ለተያያዥ ወጪዎች ብድር በቀላሉ እና በአነስተኛ ወለድ እንዲያገኙ በማድረግ ማኅበራቱ ጉልህ አስተዋጽ አበርክተዋል ብለዋል፡፡

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ሶፊያ ካሳ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የፋይናንስ አቅማቸውን ለማሳደግና የአገልግሎት ተደራሽነታቸውን ለማስፋፋት በሚያደርጉት የአደረጃጀት፣ የአሠራር፣ የአገልግሎት አሰጣጥና የህግ ማዕቀፍ ማሻሻያ ሁሉም ባለድርሻ አካላት አስፈላጊውን ድጋፍና ትብብር ሊያደርጉ ይገባል።

የኅብረት ሥራ ማኅበራት ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፣ በግብዓት አቅርቦት የማምረቻ ዋጋ በመቀነስ፣ አምራቹ ከምርቱ ተገቢውን ጥቅም እንዲያገኝ በማድረግ አስተዋጽኦ እያደረጉ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

ኅብረት ሥራ ማኅበራት የዜጎችን የተናጥል ጉልበት፣ ገንዘብና እውቀት በማሰባሰብ የግብርና ግብዓቶችና ቴክኖሎጂዎች በማቅረብ እየሠሩ መሆኑን ጠቅሰው፤ ለምርቶች የገበያ ትስስር በመፍጠር፣ የሸቀጦች ዋጋ በማረጋጋት እንዲሁም ቁጠባና ኢንቨስትመንትን በማስፋፋት በኩልም በርካታ ሥራዎችን እየሠሩ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአየር ኃይሉ አሁናዊ ቁመና የመከላከያ ሪፎርም ስኬት ማሳያ ነው!

ሀገራችን ዘመናዊ የጦር ኃይል መገንባት ከጀመረችበት ጊዜ አንስቶ በዋነኛነት ከሚጠቀሱት የጦሩ ክፍሎች አንዱ የኢፌዴሪ አየር ኃይል ነው። አየር ኃይሉ ከተመሠረተበት ከኅዳር 20 ቀን 1928 ዓ.ም. ጀምሮ የሀገርን የአየር ድንበር ከመጠበቅ አንስቶ በተለያዩ የውጊያ ዓውዶች ከፍተኛ ጀብዱዎችን በመፈጸም ለሀገርና ለሕዝብ የኩራት ምንጭ የሆነ ተቋም ነው።

ከምሥረታው እስከ 1942 ዓ.ም በንጉሡ ቀጥታ አመራር በስውዲናዊዎቹ ጄኔራል ሐርድና ካውንት ቮን ሮዛን (ኮሎኔል) አማካሪነት ሥራውን የጀመረው አየር ኃይሉ፤ ከምስረታው ማግስት ጀምሮ በሙያው አንቱታ ባተረፉ እንደ ሜ/ጄ አሰፋ አያና፣ ሜ/ጄ አበራ ወ/ማርያም፣ ሜ/ጄ ፋንታ በላይ እና ሜ/ጄ አምሐ ደስታ የተመራ ባለብዙ ገድል ተቋም ነው።

የአየር ኃይሉ ከሀገር ውስጥ ግዳጅ ባለፈ በዓለም አቀፍ የሠላም ማስከበር ሥራዎች ላይ በመሳተፍ አንቱታን ያተረፈ ነው ። ለዚህም በ1960 ዓ.ም በአራት ኤፍ 86 አውሮፕላኖች በፍላይት ደረጃ ኮንጎ ዛየር በተደረገው የሠላም ማስከበር ሥራ ላይ በቀዳሚነት ተሳትፏል። 2000 ዓ.ም ዳርፉር ሱዳን (UNAMID በኦቭዬሽን የሠላም ማስከበር ዩኒት በአምስት ሚ-35 ተዋጊ ሄሊኮፕተሮች ከተሟላ የጥገና አቅምና የድጋፍ መሣሪያዎች ጋር ተሰማርቷል። በአብየና ሩዋንዳ የሎጅስቲክና ጦር ማዘዋወር ግዳጆችን በብቃት መወጣቱን መጥቀስ ይቻላል ።

የቀድሞው የሶማሊያ አምባገነናዊ መሪ ዚያድ ባሬ በምሥራቁ የሀገራችን ክፍል የከፈተውን የመስፋፋት ጦርነት በብቃት በታላቅ ተጋድሎ ለመከላከል በተደረገው ጦርነት አየር ኃይሉ ከፍ ባለ ብቃት የፈጸማቸው ጀብዱዎች የሀገሪቱን ሉዓላዊነት በማስጠበቅ ሂደት የጎላ ስፍራ ከመያዝ ባለፈ፣ ተቋሙና ባለሙያዎቹ የብዙ ጀብዱ ትርክቶች ባለቤት እንዲሆኑ አድርጓቸዋል ።

የአየር ኃይሉ እንደ ሌሎች ሀገራዊ ተቋማት ላለፉት ስድስት አስርተ ዓመታት በተለያዩ ውጣ ውረዶች ውስጥ ለማለፍ የተገደደባቸው አጋጣሚዎች ተፈጥረዋል፤ እንደ አጀማመሩ መቀጠል የሚያስችለውን እድል ማግኘት ሳይችል በመቅረቱም ፣ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ሀገሪቱን እና ሕዝቦቿን የሚመጥን ቁመና ሳይላበስ ቀርቷል ።

ይህንን የተቋሙን ገጽታ ለመቀየር የለውጥ ኃይሉ ወደ ሥልጣን ከመጣ ማግሥት ጀምሮ ሰፊ ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል። በሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት ላይ ሁለንተናዊ ለውጥ ለማምጣት ታስቦ የሚተገበረው የመከላከያ ሪፎርም አካል የሆነው፤ የመንግሥት ጥረት በርግጥም በተቋሙ ላይ ለውጥ እያመጣ ስለመሆኑ በየዕለቱ በተጨባጭ መታዘብ እየቻልን ነው።

የአንድ ሀገር ሉዓላዊ የአየር ክልል መጠበቅ ውስብስብ እየሆነ በመጣበት በዚህ ዘመን፤ መንግሥት አየር ኃይሉን በሁሉም መስክ ብቁ በማድረግ ለሀገርና ለሕዝብ የኩራት ምንጭ እንዲሆን ከፍያለ ትኩረት ሰጥቶ መንቀሳቀሱ፣ የተቋሙ አመራሮችም አጋጣሚውን በአግባቡ በመጠቀም ተቋሙ ዘመኑን የሚመጥን/የሚዋጅ ለማድረግ በተነቃቃ መንፈስ እየሄዱበት ያለው መንገድ፤ ሀገርን እንደሀገር የማጽናት ተልዕኮ አካል ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

በአሁን ወቅት አየር ኃይሉን በትጥቅ ከማዘመን አንስቶ ብቃት ባላቸው ባለሙያዎች እንዲደራጅ የተደረገው ጥረትና በተጨባጭ እየተገኘ ያለው ስኬት፤ የሀገርን ሉዓላዊነትና የሕዝባችንን ሰላም በተሻለ መልኩ ለማስጠበቅ የሚያስችል አስተማማኝ አቅም መፍጠር ያስቻለ ነው፤ ቀደም ሲል ሕዝባችን ስለተቋሙ ባለጀብዱ ባለሙያዎች የነበረውን ከበሬታ መመለስ የሚያስችል ነው ።

ከዚህም ባለፈ በልማት ድህነትን ለማሸነፍ ለጀመርነው መነቃቃት ስኬት፤ እንደ ሀገር መፍጠር የሚገባንን በራስ መተማመን እውን ለማድረግ፤ ለወዳጆቻችንም ሆነ ለጠላቶቻችን በኛ እና በእኛ ጉዳይ የሚኖራቸው እይታ የተስተካከለ እንዲሆን ትልቅ መልእክት ማስተላለፍ የሚያስችል የዛሬ ስኬታችን አንዱ ገጽታ ነው!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ ዓምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## እንመካከር

እንዳለው ሙሉዓለም

የምክክርን ምንነት የእንመካከርን ትርጉም የአለቃ ደስታ ተክለወልድ መዝገበ ቃላት መጽሐፍ ጠቅሼ አልበይንም። ምስጢሩ ለማንም ግልጽ ነውና! ምክክር ሃሳብ ማዋጣት ነው። እንመካከር! ይህን ይቅር እንባባል፣ ይህን እንተወው፣ ይህ ጥፋት ነው፣ ይህ ደግሞ እስካሁንም ያቆየን መልካም ጎናችን ነው። እየተባባልን የሚቀጥለውን አጽንተን የሚያስቸግረውን በይቅርታ አጥፍተን የምንሻገርበት ያለ የነበረ ብሂል ነው።

ምክክር ስህተት ሲታረምበት፣ ባለጌ ሲቀጣበት ደግነት እና መልካም ሥራ ሲወደስበት የኖረ ብሂል መሆኑን ምሳሌያዊ ንግግሮቻችን ያስረዱናል። ምክክርን በተመለከተ በምሳሌያዊ ንግግሮቻችን ምን ተባለ አሁን ካለንበትስ ወቅት ጋር እንዴት ተሳሰሩ የሚለውን እንደሚከተለው በወፍ በረር እንቃኘው።

**ለሹመት ካልመከሩለት ለጥርስ ካልከደኑለት! (ለሹመት ካልመከሩለት ለጥርስ ካልነከሩለት!)**

ሥልጣንህ እንዲጠና ወንበርህ እንዳይነቃነቅ ምክክር መልካም መሆኑን ያስረዳናል። ወደታች ባለሙያዎችንን እና ወጣቶችን ወደ ላይ እድሜ ጠገብ አዛውንቶችን እና የሃይማኖት አባቶችን ማማከር ይገባል። በትይዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን፣ የሲቪክ ማኅበራትን በሌሎች መንገዶች የተቧደኑ ማኅበረሰቦችን እንዲሁም ግለሰቦችን ወደ ጎን አማካሪዎችን እና የየዘርፉ ባለሙያዎችን ማማከር ወንበርን ያረጋል።

ሥልጣንን በጉልበት ሳይሆን በፍቅር ያስቀጥላል። ለዚህም ነው ያልተመካከሩበት ሹመት ካልከደኑለት ወይም ካልነከሩለት ጥርስ እኩል የሆነው። ያልተነከረ ባቄላ ብትጎረድምበት ጥርስህ በታምር ከመነቀል ቢተርፍ መነቃነቁ እና አስቸጋሪ ሕመም ማስከተሉ አይቀርም። በዚህኛው ብናየውም ጥርስን በከንፈር ካልከለሉት በአቧራው፣ በነፋሱ ከመጎዳቱም በላይ ልቅሶ ቤት ላይ አሊያም አልሆነ ቦታ ላይ ፈገግ ብሎ ዱላ ያስመዝዝብሃል።

ገላጋይ ከተገኘ ተነቃንቆ ይተርፋል። ገላጋይም ከሌለ ጥርስህን በእጅህ ይዘህ መመለስ የመጨረሻ አማራጭህ ነው። ተመካክረንስ ቢሆን ሹመትም ደህና ጥርስም መልካም ይሆኑ ነበር። እንደ ሀገር አብሮ ፈገግ በሚባልበት አብረን ስቀን በምናዝንበት አብረን ተክዘን የጋራችን ደስታ የጋራችን ሕመም የሆነች ሀገርን መመሥረት ያስችላል።

**ባለጌ የመከሩት ዕለት ቁንጫ የጠረጉት ዕለት ይብሰዋል!**

ይህን ምሳሌያዊ ንግግር በማወቁ መሰለኝ በሀገራችን የተቋቋመው እና በሥራ ላይ ያለው የምክክር ኮሚሽን የምክክር ተሳታፊዎች በጥንቃቄ የመምረጡን ነገር ረጅም ሰዓት ሠጥቶ እየሠራው ያለ! ባለጌማ ባለጌ ነው! ለራሱ ካለመስማቱም በላይ ሲሳተፍ ነገርን ያለውሉ በማዞር ልክ ዝንብ እንደገባበት እርጎ አድርጎት ነገሩን እንዳይበላ እንዳይዘራ አድርጎት ይቀመጣል። ሁሉንም ማማከር ቦታም ጊዜም በመፈለጉ የተወሰኑ በእውነት እና በማኅበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸው አፋቸው ላይ ጨው የማይሟሟ ሐቀኛ ወኪሎችን ለምክክር ማግኘት ተገቢ ነው። ይህ ካልሆነማ **"ባለጌ ያለበት ሸንጎ ዝንብ የገባበት እርጎ!"** የሚባለውም ይሆንብናል።

በተደጋጋሚ ስለውይይት ስለ ምክክር ሲነሳ እኔም ምሳሌያዊ ንግግሮችን ጠቅሼ ሳወራ **"ምክር እና ቡጢ ለሰጭው ቀላል ነው! "**ተውን እባካችሁ ብለው ሊሞግቱን ያስባሉ። ምክክር ግን ሰጪ እና ተቀባይ የለውም። የአንተም፣ የእኔም፣ የአንቺም፣ የእሱም፣ የእሷም... ሃሳብ ይፈልጋል። ሃሳብ የሚጣለው ወይም ተቀባይነት የማይኖረው የእኔ ስለሆነ ያንቺ ወይም ያንተ ስለሆነ አይደለም።

ሃሳቡ ከሌሎች ሃሳቦች የተሻለ ሳይሆን ሲቀር ብቻ ነው። በምክክር ላይ ሃሳብ እንጂ ተናጋሪ አይወዳደርም። በምክክር ላይ ሰጪ ብቻ ወይም ተቀባይ ብቻ አይኖርም። ሰጪም ተቀባይም እንጂ የምንቀበል የጎደለንን ነው። የምንሰጥ ደግሞ ያለንን ይህ ደግሞ ምልዑነትን ያመጣል።

**ምከረው ምከረው እምቢ ካለው መከራ ይምከረው!**

ሀገራችን ይህንን ምሳሌያዊ ንግግር በሥነቃሎቿ ውስጥ አስገብታ መጠቀም ከጀመረች ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል። አሁን ባለንበት ሁኔታ ግን ከምክሩ በፊት መከራው ቀድሞናል። መከራው ሳይጠነክር አሁንም መሥራት ይጠበቅብናል። ተመካክረን ልናስቀራቸው የሚገቡ ችግሮች ጤና ነስተውናል። ድሃ አድርገውናል። ሕይወት አስገብረውናል። ምክርን እምቢ ባንልም ባለመጀመራችን መከራው አበሳችንን አሳይቶናል።

አሁንም ከእዚህ ሳይከፋ ከመከራው ሳይሆን ከክፉ መከራችን ሳንማር(መከራውንማ ጀምረነዋል) ወደ ሸንጎው ጥላ እንሰባሰብ። እንመካከር መከራውን በጥቂቱ አየነው። ጠንከር ብሎ ቢመጣ ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ መረዳቱ ቀላል ነው። ይህን ከመረዳት በላይ ደግሞ መመካከር ቀላል ነው። ከመከራው ወደ ምክክሩ የምናደርገው ጉዞ ደግሞ ያየነው የተበደልንበት ስለሆነ ውጤቱ ጥሩ እንደሚሆን አያጠራጥርም።

በመሆኑም በፍጥነት ወደ ምክክር መሄድ ለወደፊቱ ቀና እና ዋናው መንገድ ነው። አባባሉም በምክክር ያልታረመ ከችግር ከሰቆቃው እንደሚማር ይነግረናል። መቸም መከራን የሚመርጥ አይኖርም።

**ለብልህ አይመክሩ ለአንበሳ አይመትሩም!**

የአንድ ሰው አዋቂነት በአንድ ጉዳይ ብቻ ነው። ቢበዛ በሁለት፣ በሦስት ጉዳይ ተሰጥዖም እውቀትም ሊኖረው ይችላል። ሀገር ደግሞ የሁለት ሦስት ጉዳይ ብቻ ውሕድ አይደለችም። ምክክራችን ለሀገራችን ሉዓላዊነት ለሀገራችን ሥልጣኔ እስከሆነ ድረስ መምከር መመካከር ብልሁን ባይጠቅመው ምን ሊጎዳው!? የሕክምና ባለሙያዎች ስለመድኃኒት አጠቃቀም ሲያስረዱ "ተጓዳኝ ችግር የሌለው መድኃኒት የለም። ካለም ውሃ ብቻ ነው ይላሉ። "

ቢዘነጉት እንጂ ምክርም ምንም ተጓዳኝ ችግር የለውም። እንዲያውም ምክክር አንዱ የሥነልቦና ሕክምና ዓይነት አይደል። ምክክር ለጤናም አስፈላጊው መድኃኒት መሆኑ ነው። ስለዚህ የፖለቲካ ጤናችን፣ የማኅበራዊ ሕይወት ጤናችን እና የኢኮኖሚ ጤናችን ለመመለስ አሊያም ለማሻሻል ምክክር ዓይነተኛው መድኃኒት ነው።

አዎ! ብዙ ብልሆች ብዙ አዋቂዎች ምክርም ዝክርም የማይፈልጉ ይኖራሉ። እንምከራችሁ ብቻ አይደለም ሃሳባችን እንመካከር ነው። ስለዚህ ምክራችንን ባትፈልጉ ምክራችሁ ያስፈልገናል። በአንድ ጥላ እንረፍ፣ ሃሳብ እናዋጣ፣ በሃሳብ ከተቀራረብን በጉልበት የሚያግዘን ብዙ ነው። እውነትም የወጣቶች ሀገር ሆና ኃይል እና ችኩልነት ያጠቃናል። ስንቸኩል ወደ ኋላ እንዳንመለስ እንጠንቀቅ። ለጥንቃቄው መነጋገር ሃሳብ ማንሸራሸር ተገቢ ነው።

በምክክር ጊዜ ጥሩ አለመሆኑንም መግለጽ ያስፈልጋል። እንደዚህ አይሠራም። አሠራሩን ግን አላውቅም ማለትም ጥሩ ነው። መቸም የሚጣፍጠንን እና የማይጣፍጠንን ምግብ ለመለየት የምግብ ባለሙያ መሆን አይጠበቅብንም። ስለዚህ አለመጣፈጡን ከተናገርን ትክክል ነን ብለው እንዳይቀጥሉ እና ሌላ ትክክለኛ ባለሙያ እንዲያየው ያደርጋሉ። ስለዚህ የሚፈለገው የምክክር ሃሳብ አሠራሩን ማሳየት ብቻ አይደለም። እንደዚያ አለመሠራቱንም መንገር ያስፈልጋል። ሌላውንም ሌላኛው ተመካካሪ ያመጣዋል።

ችግሮቻችን በጥበብ ከያዝናቸው በብርሃን ፍጥነት የሚያልፉ ናቸው። አብረውን እንዲዘልቁ ቂም እንዲያስቋጥሩ የምናደርጋቸው በእኛው የአያያዝ ችግር ነው። ሲጀመሩ ምልክት ሲያሳዩ ብንወያይባቸው ቋሚ ቁርሾ ሳይወልዱ ባለፉ ነበር። ለእዚህም ነው። **"ተማክረው የፈሱት ፈስ አይሸትም! "የሚሉት አበው!** ችግሩ በተወሰነ ደቂቃ ነፋስ የሚጠፋ ነው። እስከዚያው የተወሰነ ዞር ማለትም ይቻላል። ይህም ባይሆን ግን ምክክር ሲኖር የፈስን ግማት ባያስቀርም አፍንጫችንን እስክንይዝ ጊዜ እና መረጃ ስለሚሰጠን ችግሩን ያስቀርልናል። እንመካከር!

# “አዲስ አበባ ከተማ የስማርት አገልግሎቶች ተምሳሌት እንድትሆን እየተሠራ ነው”

-ከንቲባ አዳነች አቤቤ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



አዲስ አበባ፡- አዲስ አበባ የስማርት አገልግሎቶች ተምሳሌት እንድትሆን በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን የከተማዋ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ። ከንቲባ አዳነች በመዲናዋ የመንግሥት ንብረትን መቆጣጠር የሚያስችል መተግበሪያን ትናንት ሥራ አስጀምረዋል።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ ያስጀመሩት መተግበሪያ የአዲስ አበባ የመንግሥት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ከአዲስ አበባ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ጋር በመተባበር ያለማው መተግበሪያው የመንግሥት ንብረትን በቴክኖሎጂ ሥርዓት ለማስተዳደር ያስችላል።

በማስጀመሪያ ሥነ ሥርዓቱ ከንቲባ አዳነች እንደተናገሩት፤ አዲስ አበባ የስማርት አገልግሎቶች ተምሳሌት እንድትሆን በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ነው። ከዚህ ውስጥ በከተማዋ የመንግሥት እና የሕዝብ የንብረት አስተዳደርና አጠቃቀም በዲጂታል ቴክኖሎጂ አሠራር እንዲተገበር የለማውን መተግበሪያ ወደ ሙሉ ትግበራ እንዲገባ ተደርጓል።

የመንግሥትና የሕዝብ ሀብትን በሥርዓት ለማስተዳደር፣ ብክነትን እና ብልሹ አሠራርን ለማስቀረት እንዲሁም ሕንፃዎችን በመመዝገብ በትክክል አውቆ ለማስተዳደርና ለመጠቀም የሚያስችለው ይህ መተግበሪያ፤ በ20 የመንግሥት ተቋማት ላይ ተሞክሮ ውጤታማነቱ ተረጋግጧል ብለዋል ከንቲባዋ፡፡

በተቀሩት የከተማ አስተዳደሩ ተቋማት ላይም ተግባራዊ እንደሚሆንም ተናግረዋል።

የአዲስ አበባ የመንግሥት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ የሱፍ ኢብራሂም በበኩላቸው፤ መተግበሪያው ለበጀትና የግዢ ጉዳዮች ውሳኔ ለመስጠት፣ ጥገና የሚያስፈልገውን ንብረት ለመለየት፣ ንብረቶች የት እንዳሉ ለማወቅና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል ያስችላል ብለዋል።

በከተማዋ መሠረታዊ የንብረት አስተዳደር ማለትም የንብረት ቆጠራ፣ የንብረት መረጃዎችን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መያዝ እና ንብረትን ከከተማው ገቢና ወጪ ጋር አያይዞ የሚሰራበት አግባብ ውስንነት ያለበት ነበር ያሉት አቶ የሱፍ፤ የለማው መተግበሪያ ሕንፃና ቋሚ ንብረት ይመዘግባል ሲሉ አብራርተዋል።

በመዲናዋ የሚገኙ የመንግሥት ንብረቶችን በአግባቡ ለመቆጣጠር እንደሚያስችል ገልጸዋል።

እንደ ዋና ሥራ አስኪያጁ ገለፃ፤ አሁን ላይ 455 ሕንፃዎችንእና 29ሺህ 462 ንብረቶች በመተግበሪያው ተመዝግበዋል። ለወደፊቱ የ668 ተቋማት አጠቃላይ ንብረት በመተግበሪያው እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡

መተግበሪያው በውስጥ አቅም እንደለማ እና ከ30 ሚሊዮን ብር በላይ ለመተግበሪያው ይወጣ የነበረውን ወጪ ማዳን ተችሏል ያሉት ደግሞ የከተማዋ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ የሶፍትዌር ዘርፍ ኃላፊ አቶ የማነ ደሳለኝ ናቸው።

# ምክክሩ ኢትዮጵያና...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

የኢትዮጵያና የአውሮፓ ኅብረት አባል ሀገራት ታሪካዊ ግንኙነት እንዳላቸው አንስተው፤ ከነበረው ጠንካራ፣ ጥብቅና ቀደምት ግንኙነት በመነሳት ግንኙነቱን በድጋሚ ለማሻሻል ከባድ አይሆንም ሲሉ አስረድተዋል፡፡

እንደ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ የአውሮፓ ኅብረት በሰው ሀብት ልማት፣ በሀብት ፈጠራና በኢንተርፕራይዞች ልማት ድጋፎችን እያደረገ ነው፡፡ ይህም በአዲስ መልክ ግንኙነትን ለማደስ በር የሚከፍት ነው፡፡

ከኅብረቱ በመልካም አስተዳደርና በዲሞክራሲ መስፋፋት ድጋፎች መኖራቸውን ገልጸው፤ የተረጋጋና ቀጣይነት ያለው እድገት እንዲመጣ ጥረቶች መኖራቸውን አመላክተዋል፡፡ የአውሮፓ ኅብረት ድጋፉ ወሳኝ የኢኮኖሚ ድጋፍ እያስገኘ መሆኑንም አያይዘው ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ ደመቀ ማብራሪያ፤ በግጭትና በተፈጥሮ አደጋዎች የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ማልማት ኢትዮጵያ በስፋት እየሰራችበት ያለ ጉዳይ ነው፡፡ ጥረቱ የተሻለ ውጤት እንዲያመጣ በጋራና በትብብር መስራት ይገባል፡፡

በተለይም ኢትዮጵያ ከአውሮፓ ኅብረት ጋር ያላትን ግንኙነት ይበልጥ ለማሻሻልና ኅብረቱና አባል ሀገራቱ የመልሶ ግንባታ ሥራዎችን እንዲደግፉ የጋራ መግባባት ለመፍጠር ዕድል እንደሚኖረው ተገልጿል።

የአውሮፓ ኅብረት አምባሳደር ሮላንድ ኮቢያ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያና የአውሮፓ ኅብረት ግንኙነት የቆየና ጠንካራ የሚባል ነው፡፡ ግንኙነቶችን በአዲስ መልክ ለማጠናከር ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡

ዘርፈ ብዙ በሆኑ ጉዳዮች የጋራ ትብብር አለ ያሉት አምባሳደሩ፤ በንግድና ኢንቨስትመንት፣ በሰለጠነ የሰው ኃይልና በዘላቂ ልማት አጋር መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ኅብረቱ በግጭት ለተጎዱ አካባቢዎች የሚሆን ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ገልጸው፤ ወደፊትም ይቀጥላል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያ ሰላም እንዲሰፍን የአውሮፓ ኅብረት ጥረቶችን እያደረገ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ በኢትዮጵያና በአውሮፓ ኅብረት የሚደረጉ ውይይቶች ግንኙነቶችን በማጠናከር ችግሮችን ለመፍታት በር የሚከፍት ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ኅብረቱ ለኢትዮጵያ ከሚያደርገው ጠንካራ የዲፕሎማሲና ፖለቲካዊ ድጋፍ በተጨማሪ ስድስት በመቶ የውጭ ንግድ መዳረሻ መሆን የቻለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

# “በለውጡ ማግስት...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ሕዝቡ ከፍተኛ ምሬት ውስጥ በነበረበት ወቅት ተከብሮ ማለፉንም አስታውሰዋል።

ዛሬ ከዚህ በተለየ ድባብ እየተከበረ መሆኑን በመጠቆም፤ ባለፉት አምስት ዓመታት በተሠሩ የልማት፣ ማኅበራዊና የፖለቲካ ሥራዎች ክልሉ የተረጋጋ ሁኔታ ውስጥ እንዲገኝ ማስቻሉን ጠቁመዋል።

ከለውጡ ማግስት አንስቶ በርካታ የልማት ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ፣ ሕዝቡ በነፃነት የሚነግድበት እና የኢትዮጵያ መልካም ገፅታ በሚገነባበት ወቅት በዓሉ እየተከበረ መሆኑን በመጠቆም ሁኔታው ያስደስተናል ነው ያሉት።

በዓሉ በኢትዮጵያ ያሉ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እንዲተዋወቁ፣ ባህላቸውን እንዲለዋወጡ፣ የአኗኗር ዜያቸውን እንዲማማሩ ያግዛል ሲሉም አክለዋል።

የበዓሉ መከበር የወንድማማችና እህትማማች እሴት እንደሚያዳብርም አመላክተዋል።

ከለውጡ በኋላ በትምህት ዘርፍ 500 የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣ 11 አዳሪ ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ 90 ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና አራት የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤቶች መሠራታቸውን አቶ ሙስጠፌ ተናግረዋል።

በጤና ዘርፍ በክልሉ ዘጠኝ ብቻ የነበሩትን የሆስፒታሎች ቁጥር ወደ 18 ማሳደግ መቻሉንም ተናግረዋል። የክልሉን የውሃ ሽፋን 18 በመቶ የነበረውን ወደ 42 በመቶ ማሳደግ መቻሉንም ነው የጠቆሙት።

በመንገድ መሠረተ ልማትም 400 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ተጨማሪ የመንገድ መሠረተ ልማት ተገንብቷል ብለዋል፡፡

# “አዲስ አበባን የሁከትና...

**ከ1ኛ ገጽ የዞረ**

ቀጣና እናደርጋለን በማለት የጥፋት ሴራዎችን አቅደው በህቡዕ ሲንቀሳቀሱ በተደረጉ የመረጃ ስምሪቶች ተረጋግጧል ብሏል መግለጫው።

በዚህ መነሻነትም ወደ ከተማዋ የታጠቁ ኃይሎችንና ቡድኖችን አስርጎ የማስገባት ሙከራ ያደረጉ ሲሆን፤ ሰልፍ እናካሂዳለን በሚል ሰበብና ሽፋን ሁከትና ግርግር በመፍጠር ንፁሐንን ኢላማ ያደረገ የሽብር ጥቃት የመፈፀም የተጠና ዕቅድ ይዘው ሲንቀሳቀሱ እንደነበር መታወቁን የጋራ ግብረ -ኃይሉ መግለጫ አመልክቷል።

ይህንን እኩይ የጥፋት ሴራ ለመፈጸም ተልዕኮ የወሰዱ 97 ተጠርጣሪዎች በተከናወኑ ኦፕሬሽኖች በቁጥጥር ስር መዋላቸውንም አስታውቋል፡፡

የጋራ ግብረ- ኃይሉ መግለጫው፤ እነዚህ ፅንፈኛ ኃይሎች እና ቡድኖች ከዚህ የጥፋት መንገዳቸው እንዲመለሱ ችግሮችና አለመግባባቶችም በውይይት እንዲፈቱ በተደጋጋሚ የተሰጣቸውን እድል ከመጠቀም ይልቅ አሁንም በሕገ-ወጥ ተግባራቸው መቀጠላቸውን አመልክቷል።መንግሥት በሀገሪቱ ብሎም በመዲናይቱ አዲስ አበባ የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ የጸጥታና የደኅንነት የጋራ ግብረ- ኃይል የማያዳግም ሕጋዊ እርምጃ እየወሰደ እንደሚገኝ ጠቁሟል።

መግለጫው አክሎም፤ የአማራ ክልል ጽንፈኛ ኃይሎች እና የሸኔ የሽብር ቡድን ታጣቂዎችን ሴራ ለማክሸፍ በአዲስ አበባ የተለያዩ አካባቢዎች የተቀናጀ ፣ጠንካራና ድንገተኛ ፍተሻ መካሄዱንና ከእነዚህ ፀረ-ሰላም ኃይሎች ጋር በትብብር የሚሠሩ ተጠርጣሪዎችም በቁጥጥር እንዲውሉ መደረጉን አመልክቷል።

ለጊዜው የተሰወሩ ተጠርጣሪዎችን አድኖ ለመያዝም የተቀናጀ ክትትልና ስምሪት እየተከናወነ መሆኑን ገልጿል።ከዚሁ ጋር በተያያዘ በተካሄደ ድንገተኛ ፍተሻም ሰርገው ወደ ከተማዋ ከገቡ ፅንፈኞችና የሸኔ ሽብር ቡድን አባላት በርካታ የጦር መሣሪያዎች፣ ተቀጣጣይ ፈንጂዎች፣ ቦንቦችና የሬዲዮ መገናኛዎችም ጭምር መያዛቸውን አስታውቋል፡፡

አንዳንድ የውጭ ኃይሎች በአማራ እና በኦሮሚያ ክልሎች በአንዳንድ አካባቢዎች የሕዝቡን ሰላም እያወኩ ያሉ ጽንፈኛ ኃይሎችንና ሽብርተኛውን ሸኔን እየደገፉ ሀገርን ለማፍረስ እያደረጉ ያለውን እኩይ ሴራ ግብረ -ኃይሉ ደርሶበታል ብሏል መግለጫው። ይህንንም ለማክሸፍ ጠንካራ ሕጋዊ እርምጃ እየተወሰደ ይገኛልም ብሏል።

የጸጥታና የደኅንነት የጋራ ግብረ- ኃይል በመግለጫው፤ የሀገሪቱን ህልውና አደጋ ላይ ለመጣል እየተንቀሳቀሱ ያሉ የውስጥና የውጭ ፀረ- ሰላም ኃይሎችና ቡድኖች ባሰቡት ልክ ወደ ተግባር እንዳይገቡና ፍላጎታቸው እንዲገታ እየተደረገ ባለው ስምሪት ተጋላጭነትን ቀድሞ በማወቅ ሊደርሱ የነበሩ ከፍተኛ ሰብአዊና ቁሳዊ ጉዳቶችን ማስቀረት ተችሏል ብሏል።በዚህ ሂደትም የጸጥታና ደኅንነት ተቋማት የነበራቸው ትብብር እንዲሁም ተቀናጅቶና ተናቦ የመሥራት ባህል የላቀ እንደነበር አመልክቷል። ኦፕሬሽኖች እንዲሳኩ ሰላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲሁም የአዲስ አበባ ሕዝብ ፀጉረ ልውጦችን፣ ሽብርተኞችንና ሕገ-ወጦችን አጋልጦ በመስጠት ያሳየው ተሳትፎ የሚደነቅ በመሆኑ ለዚህም ላቅ ያለ ምስጋናውን የጋራ ግብረ -ኃይሉ ያቀርባል ብሏል።

በቀጣይም የእነዚህን ፅንፈኛ ኃይሎች እና የሽብር ቡድኖችን እኩይ ዓላማ በማክሸፍ በኩል እየተወሰዱ ያሉ ሕግን የማስከበር እርምጃዎችን በመደገፍና ወንጀለኞችን በማጋለጥ ረገድ ኅብረተሰቡ ሲሰጥ የነበረውን ጥቆማ አጠናክሮ እንዲቀጥል የጸጥታና የደኅንነት የጋራ- ግብረ ኃይል ለኢፕድ በላከው መግለጫ ጥሪ አቅርቧል።

# ሴቶችን በማብቃት ሕፃናትን ከችግር የመታደግ መንገድ

በኃይሉ አበራ

ማዕከሉ ሕፃናትን በመታደግ ሥራዎቹ በእጅጉ ይጠቀሳል። በተለይ አሳዳጊ የሌላቸውን በርካታ ሕፃናትን ተቀብሎ እንደራስ ልጅ በማሳደግ እና ራሳቸውን እንዲችሉ በማድረግ ሥራው ይታወቃል። የማዕከሉ መሥራች በእዚህ በጎ ተግባራቸው ኢትዮጵያዊቷ ማዘር ቴሬዛ ለመባል በቅተዋል። ይህ የበጎ አድራጎት ተግባር ሀገራዊ ተምሳሌት መሆን ችሏል። ይህ ዛሬ በሕይወት የሌሉት የብዙዎች እናት እና የበጎነት ጥግ የክብር ዶክተር አበበች ጎበና የበጎነት ተምሳሌት እሳቸው በሕይወት ባይኖሩም በጎ ተግባራቸው ግን ተጠናክሮ ቀጥሏል።

እኚህ ታላቅ የሀገር ባለውለታ በርካታ ሴቶች በተለያዩ ችግሮች ሳቢያ የአብራክ ክፋይ ልጆቻቸውን ወልደው ለማሳደግ የአቅም ውስንነት እየገጠማቸው እስከመጣል ሲደርሱ ይመለከታሉ፤ ይሰማሉ፤ ሕፃናት ለሞት የሚጋለጡበት ሁኔታ ስለመኖሩም ይረዳሉ። ይህ ድርጊት በእጅጉ ያሳሰባቸው እኚህ በጎ አድራጊ በበጎ አድራጎት ድርጅታቸው አያሌ ሕፃናት ታድገዋል፤ የሴቶችንና የሀገርን ሸክምም አቅልለዋል።

የሕፃናት ችግር ከሴቶች ችግርም የሚመነጭ ነው የሚል እምነት እንደነበራቸው የሚነገርላቸው እኚህ የብዙዎች እናት፣ ሴቶችን ማብቃት የሕፃናትን ችግርም መቅረፍ ነው የሚል እምነት እንደነበራቸው ይገለጻል። በዚህ ሳቢያም ሴቶችን ከተለያዩ ችግሮች ይታደጋል ያሉትን ሴቶችን የማብቃት ፕሮግራም ያስጀምራሉ። በፕሮግራሙ በርካታ ተስፋ የቆረጡ እና መንገድ ላይ የቀሩ ለከፍተኛ ችግር የተጋለጡ ሴቶችን መታደግ ተችሏል፤ ይህም የበጎ አድራጎት ተግባር ስኬታማ ሀገራዊ ፕሮግራም እየሆነ መምጣቱን ከበጎ አድራጎት/ ቻሪቲ/ ማዕከሉ የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የአበበች ጎበና ቻሪቲ የሥልጠና ማዕከል በዚህ ፕሮግራም አማካይነት ሴቶችን የማብቃት ሥልጠና ይሰጣል፤ በየስድስት ወሩ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች ሴቶችን የማብቃት ፕሮግራም አለው። ባለፈው ሳምንት ለ36ኛ ጊዜ ያሰለጠናቸውን 130 ሴቶች አስመርቋል።

በዚህ ሥልጠና ተጠቃሚ ከሆኑት መካከል ወይዘሮ ዝናሽ ወንደወሰን አንዷ ናት። የአበበች ጎበና የ36ኛ ዙር ሰልጣኞች ተወካይዋ ወይዘሮ ዝናሽ፣ ለረጅም ጊዜ ስለ አበበች ጎበና የሴቶች ሥልጠና ስትሰማ ኖራለች። የሥልጠና እድሉን ያገኘችውም ወልዳ አራስ ቤት ባለችበት ወቅት ነው።

ወይዘሮ ዝናሽ የሥልጠና እድሉን በማግኘቷ ብትደሰትም፣ ልጅ ይዛ እንዴት አርጋ እንደምትሰለጥን ያሳስባት ጀመር። ቤተሰብ ትብብር አድርጎላት ተመዘገበች፤ ስድስት ወራት ሥልጠናውን ተከታትላም ለመመረቅ በቃች።

ሥልጠናው አምስት ዓይነት ዘርፎች እንዳሉት የምትጠቅሰው ወይዘሮ ዝናሽ፣ የልጅ እንዲሁም የቤት አያያዝ፣ መስተንግዶ፣ የባህላዊ እና ዘመናዊ የምግብ ዝግጅት ሁሉንም ባካተተ መልኩ አንድ ላይ የሚሰጥበት ነው። በውስጡም ለተቸገሩ ሴቶች የሚደረጉ ርዳታዎችን ጨምሮ የመረዳዳት እና የሰብዓዊ ድጋፎችን አስፈላጊነት የሚያስገነዝቡ ሥልጠናዎችም ተካተውበታል።

ማዕከሉ የሚሰጣቸውን የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች በሚከታተሉበት ወቅትም በቀን 33 ብር የትራንስፖርት እገዛ እንደሚያደርግ ገልጻ፣ የሥልጠና አቅርቦቶቹንና የተለያዩ ግብዓቶችን ራሱ እያሟላ ሥልጠናውን እንደሚሰጥ አመልክታለች። ከሰልጣኞቹ የሚጠበቀው ፍላጎትና ተነሳሽነት ብቻ መሆኑንም ተናግረዋል።

ወይዘሮ ዝናሽ በሥልጠናው ተጠቃሚ በመሆኗ በእጅጉ ደስተኛ ናት፤ በከሰዓት እና በጠዋት ፈረቃ ከሰኞ እስከ ዓርብ ብቻ የሚሰጥ ሥልጠና መሆኑም የማያሰላች እንዲሆን እንዳደረገው ጠቁማለች። በቡድን መሰጠቱም እርስ በርስ ለመማር እድል የከፈተ በማለት አድንቃዋለች፤ በተመሳሳይ ሌሎች በየቤቱ የሚገኙ ሴቶችም የእድሉ ተጠቃሚ እንዲሁም ጥሪ አቅርባለች።

ሴት ልጅ እንደምትችል የሚታይበት ማዕከል ነው ያለችው ወይዘሮ ዝናሽ፣ ተቀጥሮ መሥራት ብቻ ሳይሆን ራስን ችሎ ቤት ውስጥ ካለ ነገር በመነሳት መሥራት እንደሚቻል ሥልጠናው እንዳመላከታትና አቅም የፈጠረላት መሆኑንም ተናግራለች። ድርጅቱ ሰልጣኞችን ካስመረቀ በኋላም በቴሌግራም ቻናሉ በኩል የሥራ እድሎችን በመልቀቅ ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ መሆኑን በመግለጽ አመስግናለች።



ማዕከሉ ከተቋቋመ አንስቶ እስከ አሁን ሶስት ሺ 420 ሴቶችን በተለያዩ ሙያዎች አሰልጥኖ አስመርቋል፤

የአበበች ጎበና ቻሪቲ የሥልጠና ማዕከል አስተባባሪ ወይዘሮ ወይንሸት ዳምጠው ሰልጣኞቹ በተመረቁበት ወቅት እንደተናገሩት፣ ዛሬ በሕይወት በሌሉት ነገር ግን ተግባራቸው ሲታወስ በሚኖረው በሩቅ አሳቢዋና የብዙኃኗ እናት የክብር ዶክተር አበበች ጎበና የተመሰረተው ይህ ማዕከል፣ ከሚያከናውናቸው ሰብዓዊና ማህበራዊ አገልግሎቶች መካከል የምግብ ዝግጅት፣ መስተንግዶ እና የሕፃናት እንክብካቤ ማዕከል አንዱ ነው። ሥልጠናው የሚሰጠውም በሁለት ፈረቃ ለስድስት ወራት ያህል ሲሆን፤ በእያንዳንዱ ፈረቃ በሳምንት ለአምስት ቀናት፣ በቀን ለአራት ሰዓታት ሥልጠናው ይሰጣል።

በንድፈ ሃሳብ 30 በመቶ እና በተግባር 70 በመቶ በሚሰጠው በዚህ ሥልጠና፣ በባህላዊና በዘመናዊ የምግብ ዝግጅት፣ በሕፃናት እንክብካቤ፣ በመስተንግዶ፣ በእንግዳ አቀባበል እንዲሁም የሥራ ሥነ ምግባር ላይ ሥልጠናዎች ይሰጣሉ። የመግባቢያ ቋንቋ ትምህርት፣ የእሳትና ድንገተኛ አደጋ መከላከል፣ የጤና አጠባበቅ እና የሕይወት ክህሎት፣ ንግድ እንዲሁም መሠረታዊ የሕግ እውቀት ሥልጠናዎችም በፕሮግራሙ መካተታቸውንም ተናግረዋል።

ከሥልጠናው ጋር በተያያዘ በሥነ ምግባር ፕሮግራም ተጠቃሚ ከሆኑት እናቶች መካከል አንዳንዶቹ ሕፃናቱን በቀን ማቆያ (ዴይ ኬር) በማዋል የሙያ ሥልጠናውን ያለምንም ችግር እንዲከታተሉም እየተደረገ ነው፤ በዚህም በተከታታይ ስምንት ዙሮች 70 በመቶ እናቶች የእድሉ ተጠቃሚ መሆናቸውን ጠቁመዋል። ወይዘሮ ወይንሸት፣ ማዕከሉ በየዙሩ ከሰጣቸው ሥልጠናዎች ያለፉትን 15 የሥልጠና ዙሮች በተሳካ ሁኔታ ለማከናወን ሙሉ የገንዘብ እና ሃሳብ ድጋፍ ላደረገው የሜንሽን ፎር ሜንሽን ሲውዘር ላንድ ድርጅት ወይዘሮ ወይንሸት ምስጋና አቅርበዋል።

የማዕከሉ የሕዝብ ግንኙነት እና ኮሙዩኒኬሽን ማናጀር አቶ ይትባረክ ተካልኝ እንደገለጹት፤ እ.ኤ.አ በ2002 ሐምሌ ወር ሥራውን የጀመረው ይህ የማዕከሉ ፕሮግራም፣ እስከ አሁን ሶስት ሺ 420 ሴቶችን በተለያዩ ሙያዎች አሰልጥኖ አስመርቋል፤ ሥልጠናው የሰልጣኞች ሕይወት እንዲሻሻል አግዟል። ማዕከሉ በአቅም ግንባታ ሥራዎቹ በጠቅላላው ከ129 ሺህ በላይ ሴቶችን ተጠቃሚ አድርጓል። በዋናነትም ከዓረብ ሀገራት የተመለሱና ለተለያዩ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግር የተጋለጡ ሴቶችን ተጠቃሚ እያደረገ ይገኛል። እነዚህን ሴቶች በመመዝገብም በልጅ እንዲሁም በቤት አያያዝ፣ በምግብ ዝግጅት እና በሆቴል መስተንግዶ ለስድስት ወራት በማሰልጠን አብቅቷል።

ማዕከሉ ሴቶችን በተለያዩ የሙያ ሥልጠናዎች አስመርቆ መተው ብቻውን በቂ እንዳልሆነም ማዕከሉ ያምናል ያሉት አቶ ይትባረክ፣ ተመራቂዎቹ የሥራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠር የሥራ እድል የሚያገኙበትን ሁኔታም እንደሚያመቻች ነው የተናገሩት። ሥራ ያገኙ እና የማብቃት ሥልጠናዎቹን የወሰዱ አሁን በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ክትትል እንደሚደረግም ጠቅሰው፣ ባለፉት 35 ዙሮች የተመረቁት አብዛኛዎቹ ሥራ መያዛቸውንም ገልጸዋል።

ሴቶች ለስድስት ወራት ሥልጠናውን ከወሰዱ በኋላም ለአንድ ወር ያህል የሥራ ላይ ልምምድ እንዲያደርጉ ወደ ተለያዩ ተቋማት እንደሚላኩ ጠቅሰው፣ አንዳንዴም በዚያው ሥራ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዳለም ገልጸዋል። ማዕከሉ የሥራ ትስስር የሚፈጥርላቸው ሰልጣኞች እንዳሉም አመላክተዋል። የማዕከሉ ምሩቃን እይታቸው የተቀየረና መልካም ሥነ ምግባር እንዲኖራቸው እና ብቁ ባለሙያዎች እንዲሆኑ ብዙ የሚደከምባቸው መሆናቸውን ጠቅሰው፣ እነዚህን ምርጥ ባለሙያዎች የተለያዩ ተቋማት እየጠየቁ እየወሰዱ ናቸው ይላሉ።

በልጅ አያያዝ (በዴይ ኬር)፣ በሆቴል መስተንግዶ የሰለጠኑትን በር አንኳክተው የሚጠይቁ ተቋማት መኖራቸውን ጠቁመው፤ ኢንሳ፣ የኢትዮጵያ ፖስታ ድርጅት፣ የኢትዮጵያ የማህበረሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የሥራ ትስስር ከተፈጠረላቸው በርካታ ተቋማት መካከል ይጠቀሳሉ ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በሥልጠና ቆይታቸውም ሰልጣኞች በልጅ አያያዝ፣ በምግብ ዝግጅት እና በመስተንግዶ ብቻ ሳይሆን፤ በሥራ ፈጠራ / ኢንተርፕሩነርሺፕ/ ላይም የተለያዩ አጫጭር ሥልጠናዎች ይሰጣቸዋል። በዚህ መሠረትም በየጊዜው በተሰራው ጥናት እና ክትትል መሠረት ከሰልጣኞቹ ከ90 በመቶ በላይ የሚሆኑት ወደ ሥራ ገብተዋል። በቀጣይም መቶ በመቶ የሚሆኑት ሥራ እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዷል። ሥልጠናዎቹ የሚሰጡት ሙሉ በጀት ተመድቦ ሲሆን፤ መምህራንን በመቅጠር፣ ከውጭ ለሚመጡ ተጋባዥ አሰልጣኞችም ክፍያ በመፈጸም ነው። ማዕከሉ ሴቶቹን የማብቃት ሥልጠና በሚሰጠበት ጊዜ የመማሪያ ግብዓቶችን አሟልቶ እንዲሁም ለሰልጣኞቹ በቀን 30 ብር የትራንስፖርት እገዛ በማድረግ ነው።

ሕጻን ልጅ ይዘው መንገድ ላይ የሚለምኑ በርካታ ሴቶች እንዳሉ የሚናገሩት አቶ ይትባረክ፣ እነዚህ እናቶች ወደ ማዕከሉ መጥተው ይህን እድል መጠቀም የሚችሉበት ሁኔታ ቀደም ሲል እንዳልነበረም ያስታውሳሉ። ማዕከሉ ይሄንን ችግር በመረዳት በማዕከሉ ከአምስት ዓመት በፊት የሕፃናት ማቆያ / የዴይ ኬር/ ማዘጋጀቱን ገልጸዋል። ይህ ሁኔታ እናቶች ለሥልጠና ወደ ማዕከሉ ሲመጡ ልጃቸውን ይዘው እንዲመጡ፤ ሲወጡም ልጃቸውን ይዘው እንዲወጡ የሚያስችል ሁኔታ መፍጠሩን አስታውቀዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ማዕከሉ አሁን እስከ 12 ሕፃናትን ብቻ የሚይዝ የሕፃናት መዋያ /ዴይ ኬሩ/ ነው ያለው፤ ይሁንና ይህ ብቻውን በቂ አይደለም፤ አሁንም በልጅ ምክንያት ሥልጠናውን የማይወስዱ ሴቶች መኖራቸውን ጠቁመዋል። ማዕከሉ ተጨማሪ በጀት ካገኘም በርካታ በሕፃናት ምክንያት የመሰልጠን እድሉን መጠቀም ያልቻሉ እናቶችን ተቀብሎ ለማብቃት እና ሥልጠናውንም መከታተል ላልቻሉት እድል ለመስጠት ይፈልጋሉ።

ብዙ መሥራት የሚችሉ ወጣት ሴቶች ልጆቻቸውን እያሉ እና ልጆቻቸውን በክፍያ ሕፃናት ማቆያ /ዴይ ኬር/ ማቆየት ስለማይችሉ ልጅ ይዘው ይቀመጣሉ ያሉት አቶ ይትባረክ፣ እነዚህ እናቶች ልጅ የሚይዝላቸው ቢያገኙ ተሯሩጠው ሰርተው ልጃቸውን ማሳደግና መንከባከብ ይችላሉ ብለዋል። በዚህ ላይ መንግሥትም ሆነ ሌላ የልማት አጋር ድርጅቶች በስፋት ሊሰሩ እና እገዛ ሊያደርጉ እንደሚገባም ጠቁመዋል። ቢያንስ በተመጣጣኝ ዋጋ የሕፃናት ማቆያ /የዴይ ኬር/ አገልግሎቱ ቢስፋፋ እና አበበች ጎበና ቻሪቲ ማዕከል በመሳሰሉት ደግሞ በነጻ አገልግሎቱ በስፋት ቢኖር የተሻለ ለመሥራት እንደሚቻል አመላክተዋል።

የአበበች ጎበና ቻሪቲ የሥልጠና ማዕከል ከዚህ በፊት በአንድ ጊዜ እስከ 200 ሴቶችን አሰልጥኖ ማብቃት ደረጃ ላይ መድረሱን አስታውሰዋል። በኮሮና ወቅትም እንደ ሜንሽን ፎር ሜንሽን እና ዶምቦስኮ ከመሳሰሉት ድርጅቶች በሚያገኘው ፈንድ ሲሰራ እንደነበር አስታውሰዋል።

እንደ ሀገር የበጎ ሥራዎቹ ለማስፋት የበጀት እጥረት እና የአቅርቦት ችግር መኖሩን ጠቁመዋል። የበጀት ችግሩ እና የአቅድ ችግሮች ቢቀረፍ ማዕከሉ የረጅም ጊዜ ልምዱን ተጠቅሞ ሀገራዊ በጎ ተግባሩን ወደ ሌሎች ክልሎችም የማስፋት ፍላጎቱ አለው ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ማዕከሉ ሴቶችን በእነዚህ ሙያዎች አሰልጥኖ የማብቃት ዑደቱም ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ለቀጣይ 37ኛ ዙር ሴቶችን መዝግቦ የማብቃት ሥራውን እየቀጠለ ነው። ይህ ማዕከል ብቻውን በሴቶች ላይ የሚደርሱ ችግሮችን ሊፈታ አይችልም፤ ሌሎች ድርጅቶችም ይሄንን ተምሳሌትነት በመውሰድ ሴቶችን የማብቃት ሥራውን ማስፋት ይገባቸዋል።

የማህበረሰቡ ችግሮች አንድም በሴቶች ላይ ከሚደርሱ ችግሮች እንደሚመነጭ ጠቅሰው፣ ሌሎች የበጎ አድራጎት ድርጅቶች ሀገራዊ የበጎነት ሥራቸውን በዚህ ላይ ካጠናከሩ ሀገሪቱና ማህበረሰቡ በብዙ መልኩ ይጠቀማሉ የሚል እምነት እንዳላቸውም ተናግረዋል። ሆቴሎች እና ሌሎች ተቋማትም ተመራቂ ሴቶችን በመቅጠር እንዲተባበሩም ጠይቀዋል።

የሜንሽን ፎር ሜንሽን ስዊዘርላንድ የኢትዮጵያ ተጠሪ አቶ ጌታቸው ዘውዱ በበኩላቸው እንደተናገሩት፣ ድርጅቱ ለአበበች ጎበና ቻሪቲ የሥልጠና ማዕከል በዋናነት የሚያደርገው ድጋፍ ወላጆቻቸውን ያጡ ታዳጊ ሕፃናት ቤተሰብ ውስጥ ሆነው ሲያድጉ ሊያገኙ የሚገባቸውን እንዲያገኙ ለማድረግ የሚረዳ ነው። እንዲማሩ፣ ጤንነታቸው እንዲጠበቅ እንዲሁም ሌሎች የሚያስፈልጋቸው ግብዓት እንዲሟሉላቸው ይደረጋል። በየስድስት ወሩ እየሰለጠኑ የሚወጡ በትንሹ ከ140 የማያንሱ በአብዛኛው ከዓረብ ሀገር ተመላሽ የሆኑ ሴት እህቶችን በሙያ በማብቃትም ራሳቸውን ችለው ለሀገርም ለወገንም ለቤተሰቦቻቸውም እንዲተርፉ ድርጅቱ እገዛ እያደረገ ይገኛል።

በማዕከሉ ባለው ተጨማሪ ፕሮግራሙም ማዕከሉ በሚገኝበት አካባቢ ኑራቸው ዝቅተኛ በሆኑና ልጆቻቸው ከሶስት ዓመት በታች የሆኑ ለመወንጨር የተጋለጡ ሕፃናትን የመታደግ ሥራም ይሰራል። በተለይም በአሳሳቢ ሁኔታ ላይ ያሉ የቀነጨሩ፣ የጤንነት እና የምግብ እጥረት ያለባቸው ሕፃናትን በስድስት ወር ውስጥ እንደማንኛውም ሕጻን ሊኖራቸው የሚገባውን ክብደት እንዲያገኙ በማድረግ የመመገብ ሥራ እያከወነ መሆኑንም ተናግረዋል። መቀለብ ብቻም ሳይሆን ቤታቸው ይዘው የሚሄዱትን ስንቅ በመስጠት፣ ወደ ማዕከሉ በመጡ ቁጥር ልጆቻቸውን በትናንሽ ነገሮች እንዴት መመገብ እንደሚገባቸው በሙያው በሰለጠኑ ባለሙያዎች የትምህርት አገልግሎት እንደሚሰጣቸው ገልጸዋል።

በዚህም በአበበች ጎበና ማዕከል ብቻ በዓመት በአማካኝ ከ300 ያላነሱ ሴቶች ሲመረቁ በተመሳሳይ መልኩም ከ300 ያላነሱ ሕጻናት በምገባ ፕሮግራም ውስጥ ያልፋሉ ብለዋል። በምገባ እና በሥልጠና ፕሮግራሞቹ እንዲሰሩም የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል። ቡራዩ በሚገኙ ሕጻናት መዋያዎች ለሚገኙትም ድጋፍ እንደሚደርግ አስታውቀው፣ ሜንሽን ፎር ሜንሽን ድርጅት ከአበበች ጎበና ጋር ከሚሰራው ውጪም በኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም ክልሎች ላይ ሰፊ የበጎ ተግባር ሥራዎችን እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## በፈተና የፀና ህይወት

ክብረአብ በላቸው

ሕይወት በብዙ ፈተና እና ትግል ውስጥ የምናልፍበት ተግባራዊ ትምህርት ቤት ነው። በዚህ የፈተና ሕይወት ውስጥ ብዙዎች ሲወድቁ አንዳንዶች ግን በድል ይወጡታል። የሕይወት ፈተና ወደ መሬት ሲጥለን በወደቅንበት ቦታ ሆነን ማማረር፤ ማጉረምረም፤ ለመውደቁ ፤ ለመደናቀፉ ምክንያት የሆኑትን ሰዎች ሁኔታዎች እና እድለቢስነቱን ማማረር ሳይሆን ከወደቁበት ለመነሳት መሻት ብቸኛው መፍትሔ ስለመሆኑ እሙን ነው።

የዚህች ዓለም ውጣ ውረድ፣ ቁልቁለት እና አቀበቱ፣ የሕይወት ውስብስብ ፈተና አያልቅም። ሁሌም ቢሆን በሕይወት ውስጥ ክፍተት አለ። ሁልጊዜ ደስተኛ መሆን አይቻልም። አንዳንዴ መከፋት፣ ሀዘን ይኖራል፤ አንዳንዴም ማጣት ይከሰታል፣ ሁሉም ነገር አይሰጥም ሁሉም ነገር ደግሞ አይታጣም። በሕይወት ውስጥ ሁሌም ክፍተት አለ፤ ሕይወት ያመጣችውን ፈተና ተጋፍጦ ውጤታማ መሆን ለብርቱዎች የተሰጠ ፀጋ ነው።

ጋዜጠኛ ፍሬሕይወት ትባላለች። ተወልዳ ያደገችው በጅማ ከተማ ነው። የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን በትውልድ ከተማዋ ጅማ ተከታትላለች። በመቀጠልም ከቤተሰቦቿ ጋር ወደ ወሊጋ ጊምቢ በማምራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን መከታተል ችላለች። በትምህርት አቀባበሏ በመካከለኛ ደረጃ ከሚመደቡ ተማሪዎች መካከል እንደነበረች የምትናገረው ፍሬሕይወት በጊምቢ የጀመረችውን የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በአዲስ አበባ ከተማ በመጠናቀቅ ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በመቀላቀል በኮምፒውተር ሳይንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ማግኘት ችላለች።

በጅማና ጊምቢ ቆይታዋ በከተሞቹ ባሉ የሰርከስ የስፖርት ቡድኖች ውስጥ ንቁ ተሳታፊ የነበረችው ፍሬሕይወት በአዲስ አበባ ከተማም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን እየተከታተለች በሙዚቃ፣ በቴሌቪዥን ድራማና በሬዲዮ ፕሮግራሞች ላይ ትሰራ ነበር። ከዚህ በተጨማሪ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ በነበረችበት ወቅት በ2001ዓ.ም በአዳማ ከተማ ወይዘሪት ሚሊንየም ተብላ የቁንጅና ውድድር አሸናፊ መሆን ችላለች።

ለጋዜጠኝነት ያላት ፍቅር ከፍተኛ እንደሆነ የምትናገረው ፍሬሕይወት ይህንን ህልሟን ለማሳካት ጠንክራ በመሥራት ወደ ኦሮሚያ ብሮድካስቲንግ ኔትወርክ (ኦ. ብ. ኤን) ተቀላቅላ ሪፖርተር፣ ዜና አንባቢ፣ ብሎም ፕሮግራም አዘጋጅ በመሆን በምትወደው ሙያ ጥቂት ለማይባሉ ዓመታት አገልግላለች። ከጋዜጠኝነት ሥራዋ ጎን ለጎን በድራማ፣ በማስታወቂያ፣ በመድረክ ትርኢት እና በሞዴሊንግ ለረዥም ጊዜ መሥራት ችላለች።

የፍሬሕይወትን የሕይወት አቅጣጫ የቀየረው ክስተት የተከሰተው በ2006 ዓ.ም ለሥራ ጉዳይ ከአዳማ ወደ አዲስ አበባ ከተማ መጥታ የነበራትን ሥራ አጠናቅቃ ወደ አዳማ ከተማ በመመለስ ላይ ሳለች የመኪና አደጋ ይደርስበታል። በደረሰባት የመኪና አደጋ አንድ እግሯን ያጣችው ጋዜጠኛ ፍሬሕይወት በወቅቱ የተፈጠረውን አጋጣሚ ስታስታውስ ሁኔታው እጅግ አስቸጋሪ እንደነበር ትናገራለች፤ “አብረውኝ የነበሩ ጓደኞቼ እንዲሁም አንድ የ8 ወር ነፍስ ጡር ሴት ምንም አልሆነችም ሁሉም ጭረት አልነካቸውም ነበር” ትላለች።

የደረሰባትን አደጋ ስትገልጽ “ህልም ነበረ የመሰለኝ” የምትለው ፍሬሕይወት፤ በወቅቱ ከአደጋው ትንሽ ቆይቼ ስነቃ እኔ ብቻ ነኝ ከመኪና ስር ያለሁት ከውጭ ፍሬሕይወት የሚል የለቅሶ ድምጽ ሰማሁ። እንደምንም ብዬ ልወጣ ስል አንድ እግሬ ከፊት ወንበር ስር አስገብቼ ነበረና እግሬ ተጎድቷል። ሳየው አንድ እግሬ ተንጠልጥሎ አገኘሁት። ስትል እጅግ አስቸጋሪና መጥፎ የነበረውን አጋጣሚ ታስታውሳለች።

ይህንን አደጋ አሸንፌ ዛሬ ላይ ውጤታማ መሆን እንድትችል ስላደረጋት የሕይወት ሚስጢር ስትናገር፤ “ምንም ነገር በሕይወቴ ሲከሰት ለበጎ ነው የሚል እምነት አለኝ። በተጨማሪም በፈጣሪ ላይ ትልቅ እምነት አለኝ። ተስፋ ስለመቁረጥ አስቤ አላውቅም። ምንም ነገር በሕይወቴ ስመጣ ለመልካም ነው የሚሆነው የሚል አመለካከት ከድሮ ጀምሮ ስላለኝ ነው። ከዚህ በሻገር በደረሰው አደጋ የተጎዳሁት እኔ ብቻ መሆኔ ይህ በእኔ ላይ የደረሰው ፈጣሪ የሆነ ምክንያት ስላለው ነው ብዬ ለመቀበል ብርታት ሆኖኛል” ትላለች።

ሰው ከተወለደበት ጊዜ ጀምሮ የሚገነባበት የተለያየ




መንገድ አለ የምትለው ፍሬሕይወት፤ ከቤተሰብ፣ ከማህበረሰብ፣ ከትምህርት ቤት፣ ከውሎ ብዙ መማር ይቻላል፤ ትላለች። ከልጅነት ጀምሮ ፈተናዎችን አልፈው ስኬታማ መሆን የቻሉ ሰዎችን ታሪክ ማየት እንደሚያስደስታት ፈተና ገጥሟቸው ያንን ፈተና እንዴት አለፉ ብላ እንደ ሰዓሊ ብሩክ የሺጥላ፣ የትነበርሽ ንጉሴ፣ መጋቢ ሀዲስ እሸቱ ዓይነት በሕይወታቸው ፈተና ገጥሟቸው በፅናት ታግለው አሸናፊ መሆን የቻሉና ስኬት ያስመዘገቡ ኢትዮጵዊያንን ሕይወት መከታተሏ ለሰው ልጅ ከአካል በላይ ትልቁ ነገር አዕምሮና ስብዕና ነው የሚል መረዳት ፈጥሮ በሕይወቷ ውስጥ የተከሰተውን ፈተና ማለፍ እንድትችል ብርታት እንደሆናት ትናገራለች።

ምንም ነገር በሕይወት ስመጣ ፈጣሪ ፈቅዶ የሚሆን ነው ብላ እንደምትቀበል የምትናገረው ፍሬሕይወት፤ ነገሮችን ለበጎ ነው ብለን ካሰብን ለበጎ ይሆናሉ። ሕይወት ያስተማረችንም ይህንን ነው ትላለች። ትላንትና ሙሉ አካል ነበርኩኝ ዛሬ አካሌ ጎድሎ እንዴት ጓደኞቼ ጋር እቀርባለሁ? እንዴት ወደ ሥራዬ እመለሳለሁ? ቤተሰቦቼስ ምን ይላሉ? የሚሉ አሉታዊ አስተሳሰቦችን መጋፈጥ የግድ ነው። በሕይወት ውስጥ መቀየር የማንችላቸው ነገር ወደ ሕይወታችን ሲመጣ ያንን ነገር በማዘን፣ በመጨነቅ እንዴት ይህ ነገር በእኔ ላይ ሆነ እያሉ መለወጥ የማይችሉት ነገር ውስጥ ከልቆዩ የትኛውንም ፈተና ማሸነፍ ይቻላል ትላለች።

ፍሬህይወት እንደምትናገረው፤ “እግሬ መቆረጡን አምኜ ስወስን ወደ እኔ ሊመጡ የሚችሉ ሃዘኔታ የሚመስሉ ግን እኔን የሚሰብሩ ወይም መንገድ ላይ የሚያስቀሩ ንግግሮችን ከንፈር መጠጣን ጨምሮ መዘጋት እንዳለብኝ እራሴን በማሳመን ሆስፒታል በነበርኩ ሰዓት አንድም ቀን ለሰከንድ ፈገግታ ከፊቴ ተለይቶ አያውቅም። አዝነው ለጥያቄ የሚመጡ ቤተሰቦቼን፣ የሥራ ባልደረቦቼን ሁሉ እግር ነው ያጣሁት እስትንፋሴን አለጣሁም፤ እግር ደግሞ የሚተካ ነገር ነው፤ ምንም ማለት አይደለም እያልኩ ቀላል አድርጌ እነግራቸዋለሁ። አልቅሰው የመጡ ሰዎች እኔን ሲያዩ እንባቸውን ይገቱ ነበር” ስትል ትናገራለች።

በራስ አቅም መፍታት የማንችለው ችግር ሲያጋጥመን ከዛ ነገር ቶሎ አዕምሮን ማውጣት አስፈላጊ ነው የምትለው ፍሬሕይወት፤ “በማዘን፣ በመቆጨት፣ በማላዘን፣ በማልቀስ እራሳችንን ብሎም በዙሪያችን ያሉ ሰዎችን ሁሉ ስለሆነ የምንጎዳው ወዲያው ከዛ ስሜት ወጥቶ ቀሪ ሕይወትን ለማስተካከል መጣር ተገቢ ነው። እኔም የገጠመኝን ፈተና ተሻግሬ ዛሬ ላይ መቆም የቻልኩት ይህንን የሕይወቴ መርህ ስላደርኩት ነው” ትላለች።

ፈተናዎች ቢገጥሟትም የጽናት እና የቁርጠኝነት ምስክር ሆነ በጋዜጠኝነት መሰል ሥራዎች እና ችግሮችን ለማሸነፍ ባላት አቅም ሌሎችን ማነሳሳቷን የቀጠለችው ፍሬሕይወት፤ በቅርቡ፣ በአውስትራሊያ ውስጥ በተካሄደው (focus on ability) በተሰኘው ዓለም አቀፍ የአጭር ፊልም ፌስቲቫል ላይ ተሳትፋ፤ ስለ ሕይወቷ ታሪኳ ባሳየችው የሁለት ደቂቃ ከ40 ሰከንድ ቪዲዮ (አጭር ፊልም) የ5,000 የአሜሪካን ዶላር ሽልማት አግኝታለች። በተጨማሪም አምስት ነፃ የበይነ መረብ የትምህርት እድሎች ማግኘት ችላለች። ሽልማቷን በቅርቡ በኢትዮጵያ በድርጅቱ ተወካዮች በኩል ትቀበላለች።

የአጭር ፊልም ውድድሩ ትኩረት የሚያደርገው በአካል ጉዳተኞች አለመቻል ላይ ሳይሆን መቻላቸው ላይ ነው የምትለው ፍሬሕይወት፤ አካል ጉዳት ከዓላማ ማስቀረት እንደማይችል እና አካል ጉዳት ያለባቸው ሰዎች መሥራት እንደሚችሉ ማሳያ የሚሆን ፊልም ነው ለውድድር የሚቀርበው ትላለች።

የአጭር ፊልም ውድድሩ የዛሬ ዓመት አካባቢ በኢትዮጵያ የተዘጋጀ ጊዜ በተጋባዥነት ተገኝቼ ነበር የምትለው ጋዜጠኛ ፍሬሕይወት፤ ይህ ነገር የእርሷንም ታሪክ የሚወክል በመሆኑ በዚህ ዓመት በተካሄደው ውድድር አጭር ቪዲዮ ለውድድር አዘጋጆቹ በመላክ ተሳትፎ እንዳደረገች ታስረዳለች።

ድምፅ እንዲሰጥባቸው ከመላው ከተመረጡ 134 አጭር ፊልሞች ውስጥ አንዱ መሆን የቻለው የፍሬሕይወት ፊልም በአንድ ሳምንት ውስጥ ድምፅ እንዲሰጥበት ተደርጎ በአብላጫ ድምፅ ዓለም አቀፍ አሸናፊ መሆን እንደቻለ ትናገራለች። የፊልሙ የግምገማ መስፈርት የበይነ መረብ ላይ የሕዝብ ድምፅ ብቻ ሳይሆን እንደ ቀረጻ፣ አርትዖት እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚያካትት በባለሙያዎች የሚመረጥ እንደሆነ በውድድሩ ላይ ያሳየችው የሕይወት ታሪኳ ተፅእኖ ፈጣሪ ሆኖ አሸናፊ ስለመሆኑ ገልፃለች።

በአሁኑ ወቅት ፍሬሕይወት በግሏ በተለያዩ የሙያ ሥራዎች ላይ ተሳትፎ እያደረገች ትገኛለች። ከቀድሞ የሥራ ባልደረቦቿ ጋር በመተባበር (ማይሎ) የተባለ የግል የመልቲሚዲያ ኩባንያ በመቋቋም፣ በዛ ውስጥ የማስታወቂያ ሥራዎችን፣ የፌስቲቫል ፕሮግራሞችን፣ ዘጋቢ ፊልሞችን፣ የመድረክ ዝግጅቶችን እና ሌሎችንም ሥራዎች በኦሮምኛ እና በአማርኛ ቋንቋዎች በማዘጋጀት ላይ ትሰራለች። ፍሬሕይወት (ከማይሎ) ጋር ከምትሰራው ሥራ በተጨማሪ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠናዎችን በመስጠት እየሰራች ትገኛለች።

ፍሬሕይወት የወደፊትን እቅዷን ስትናገር፤ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተመርቀው እንደተከፈቱት ዓይነት የተለያዩ የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ሕፃናትና ዜጎች የሚሆኑ ድጋፍ ሰጪ ተቋማትን ለማቋቋም በትጋት ለመሥራት እቅድ እንዳለት ትገልፃለች። በትጋት በመሥራት እነዚህ ልጆች በአካል ጎዶሎነት ያጡትን እድል ዳግም የዕድሉ ባለቤት በማድረግ እና የተለያዩ የግንዛቤ መስጫ መድረኮችን በመዘጋጀት ለመሥራት የረዥም ጊዜ እቅድ እንዳላት ትናግራለች።

በተጨማሪም ፍሬሕይወት የሰው ሠራሽ የሰውነት ድጋፍን እንዴት መጠቀም እንደሚገባ ስላለውም ጥቅም ግንዛቤዎችን ለማህበረሰቡ ለማስጨበጥ፤ ሥልጠናዎችን በማዘጋጀትና እና ያሉትን የሕይወት ልምድ ለወጣቶች ለማካፈል በቁርጠኝነት እንደምትሰራ በአፅንዖት ትናገራለች። በተጨማሪም ከእሷ የሕይወት ተሞክሮ በመነሳት ታሪኳን በማካፈል ሌሎች ሰዎች መሰናክሎችን እንዲያሸንፉ እና ግባቸውን እንዲያሳኩ የማድረግ አላማ እንዳላት ትገልፃለች።

ወጣቶች ሊያጋጥሟቸው የሚችሏቸው ተግዳሮቶች እና ማዘናጊያዎች ቢኖሩም፣ ጠንክሮ እንዲሰሩ እና ተስፋ እንዳይቆርጡ በአፅንኦት የምትናገረው ጋዜጠኛ ፍሬሕይወት፤ በተለይ ወጣቶች የማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማቸው ለራሳቸው ጥንቃቄ የተሞላበት መሆን እንዳለበት ተናግራ፤ ለማህበረሰቡ የሚጠቅመውን ብቻ በመውሰድ በማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀማቸው አስተዋይ እንዲሆኑ ትመክራለች። እራስን ጠንካራ መሠረት መጣል ከልጅነት ጀምሮ እንደሚጀምር የምትናገረው ፍሬሕይወት፤ ነገ በባከነ ትላንትናቻው ላለመቆጨት ወጣቶች ጊዜያቸውን በአግባቡ ተጠቅመው ውጤታማ ለመሆን ነገ ሳይሉ ዛሬ ላይ ጠንክረው መሥራት እንዳለባቸው ትናገራለች።

ፍሬሕይወት በተጨማሪ ስትናገር፤ ወጣቶች ከእርሷ ተሞክሮ በመውሰድ መማር እና ምንም ነገር ላለመሳካቱ ሰበብ ባለመስጠት ጠንክሮ መሥራትን ብቻ አማራጭ ሊያደርጉ እንደሚገባ ተናግራ፤ ምንም ዓይነት ሁኔታ ቢያጋጥማቸው ማንኛውንም ሁኔታና መሰናክል ማሸነፍና ለስኬት መብቃትን የሕይወት መርህ በማድረግ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ትናገራለች።

ሁሉም ሰው በሕይወት ሲኖር የሚያልፈው የተለያየ የሕይወት ምዕራፍ አለው የምትለው ፍሬሕይወት፤ ከደረሰባት አደጋ የተማረችው ነገር ቢኖር በሕይወት ውስጥ ነገ የሚባል ቀን እንደሌለ ነው። የተሰጠን ቀን ዛሬ በመሆኑ ነገ በእኛ እጅ ስላይደለ ዛሬን በአግባቡ መጠቀም እንዳለብን ነው። ስለዚህ ዕድሜያችንን በአግባቡ ሰዓት እንጠቀም ፤ ቀናቶቻችንን ባለማባከን ለጥቅማችን ማዋል አለብን ከምንም በላይ ደግሞ በፈጣሪ ላይ ትልቅ እምነትና ተስፋ ሊኖረን ይገባል ስትል መልዕክቷን አስተላልፋለች።

# የታጠበ የድንጋይ ከሰል አምራቹ ፋብሪካ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ኢትዮጵያ በማዕድን ሀብት የታደለች ሀገር ናት። ቀደም ባሉት ጊዜያት ይህንን የማዕድን ሀብት አልምቶ ጥቅም ላይ በማዋል ረገድ እምብዛም አልተሰራም፤ ማዕድናት በጥናት ለመለየት በተከናወነ ተግባር እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በጥናት የተለዩት ማዕድናት 30 በመቶ ብቻ መሆናቸው፣ በሀገሪቱ የማዕድን ጥሬ እቃዎች እያሉ ከውጭ እየገቡ ያሉበት ሁኔታም ይህንኑ ያመለክታሉ። በወርቅ በኩል ከሚታዩ ውስን የማልማት ሥራዎች ውጭ ብዙ ርቀት የተሄደበት ሁኔታ የለም። እሱም ብዙም ባልዘመነ መልኩ ሲካሄድ ነው የቆየው።

መንግሥት በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው ለማዕድን ዘርፉ የሰጠውን ትኩረት ተከትሎ ግን በዘርፉ ለውጦች እየታዩ ናቸው። ከእነዚህ ለውጦች መካከልም በድንጋይ ከሰል ማዕድን ላይ እየተካሄደ ያለው ልማት ይጠቀሳል። በእዚህ ልማት ሀገሪቱ ባለፈው ዓመት ከውጭ ማስመጣት የነበረባትን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ መሸፈን ችላለች።

በድንጋይ ከሰል ልማቱ በርካታ ዜጎች በማህበራት ተደራጅተው እየሰሩ ሲሆን፣ የድንጋይ ከሰል ልማቱን በኩባንያ ደረጃ ለማካሄድ ወደ ስድስት የሚደርሱ ኩባንያዎች ፈቃድ ወስደው እየሰሩ ስለመሆናቸው መረጃዎች ይጠቁማሉ።

ከእነዚህ ኩባንያዎች ውስጥ አንዱ «ዮ ሆልዲንግ ንግድ እና ማኑፋክቸሪንግ» የተሰኘው ሀገር በቀል ድርጅት ነው። ድርጅቱ ዮ ሆልዲንግ በተሰኘው ድርጅቱ በማዕድኑ ዘርፍ በመሰማራት ኢትዮጵያ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ በማውጣት ከውጭ የምታስገባውን የታጠበ የድንጋይ ከሰል የሚተካ ምርት ፋብሪካ አቋቁሞ የድንጋይ ከሰል እያመረተ ይገኛል።

የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ያነጋገራቸው የድርጅቱ የአቅርቦት ሰንሰለት ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ ፍቅሬ እንዳሉት፤ «ዮ ሆልዲንግ»፤ የታጠበ የድንጋይ ከሰል ማምረት የሚያስችለውን ፋብሪካ የገነባው በ2014 ዓ.ም ነው፤ ይህ በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል በከማሼ ዞን በወሪንቃሃ ቀበሌ የተገነባ ፋብሪካ፣ በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የድንጋይ ከሰል እጥበት ማከናወኛ ፋብሪካ ነው።

ፋብሪካው የደንበኞችን ፍላጎት መሠረት ባደረገ መልኩ የታጠበ የድንጋይ ከሰል ለሚፈለገው ዓላማ እንዲሆን አድርጎ አምርቶ ማቅረብ የሚችልበት አቅም አለው ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ለሲሚንቶ፣ ለብረት፣ ለወረቀት፣ ለሴራሚክ፣ ለጂፕሰም እና ለሌሎች ፋብሪካዎች ግብዓትነት የሚውል የታጠበ የድንጋይ ከሰል በማምረት ለተለያዩ ፋብሪካዎች እያቀረበ ይገኛል ብለዋል።

ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ የድንጋይ ከሰል የማምረት ሥራውን በቀን ለ16 ሰዓታት እያካሄደ ሲሆን፣ በሰዓት 150 ቶን የድንጋይ ከሰል እያጠበም ይገኛል። ይህ ምርት ካለው ፍላጎት አኳያ በቂ ስላልሆነ የሚያመርተውን የታጠበ የድንጋይ ከሰል መጠን በእጥፍ የሚያሳድጉ ሥራዎችን እየሰራ ነው። ለእዚህ የሚያስፈልጉ እቃዎች ከውጭ እንዲገቡ እየተደረገ ነው።

ፋብሪካው ወደ ሥራ የገባው ከሁለት ዓመት በፊት መሆኑን አቶ ቴዎድሮስ ጠቅሰው፣ በአካባቢው በነበረው የጸጥታ ችግር ምክንያት በሚፈለገው ፍጥነት ወደ ሥራ ለመግባት እንዳልቻለ አሁን ግን ወደ ማምረት ሥራው መግባቱን ይናገራሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ድርጅቱ ፋብሪካ ያቋቋመበት አንዱ ዋና ዓላማ በሥሩ ላሉት ብዙ ፋብሪካዎች ለግብዓትነት የሚያስፈልገውን የድንጋይ ከሰል በሀገር ውስጥ ለማምረት ነው። ካሉት ፋብሪካዎች ውስጥ አንዱ «ኢሲኤንድ ኢ» የተሰኘው የብረት ማምረቻ ፋብሪካ ሲሆን፤ ለፋብሪካው የሚሆነው ጥሬ እቃ ግብዓት ከውጭ በማስመጣት እና በማቅለጥ የተለያዩ ፌሮዎችን ሲያመርት ቆይቷል።

የታጠበ ድንጋይ ከሰል የማምረቱ ሥራ የድንጋይ ከሰሉ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ውጪን ስለሚጠይቅ በዚህ ዙሪያ የሚያጋጥመውን ተግዳሮት ለመፍታት ግብዓቱን ሀገር ውስጥ በማምረት ብረት ከውጭ ማስገባት ለማቆም በማሰብ የተገባበት ነው።

በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች በብረት ማዕድን ፍለጋ ላይ በሰፊው ተሰርቶ እንደነበር ጠቅሰው፣ ይህም የፍለጋ ሂደት ብረት ከብረት ማዕድን አፈር ለማምረት ያለመ ነበር ይላሉ። ማዕድን ለማምረት ደግሞ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ያስፈልጋል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ብረቱን ከአፈር ለመለየት በሚደረገው የማቅለጥ ሂደት ከፍተኛ መጠን ያለው ኃይል ስለሚያስፈልግ አሁን ባለው የመብራት ኃይል ይህን ማዕድን ለማቅለጥ የሚታሰብ አይሆንም ሲሉ ይገልጻሉ። ስለዚህ ይህንን ኢነርጂ ሊተካ የሚችለው ብቸኛው ኃይል የድንጋይ ከሰል ነው። ብረትን እያቀለጡ ወደሚፈለገው ምርት ለመቀየር የሚቻለው በድንጋይ ከሰል ኃይል አማካኝነት ነው ሲሉ ያብራራሉ።

ድርጅቱ ወደ ድንጋይ ከሰል ማጠብ ሥራ የተሰማራበት ሌላው ዋንኛ ምክንያት ወደፊት እንደ አፍሪካም ሆነ እንደ ሀገር ትልቅ ኩራት የሆነ ከብረት ማዕድን የተለያዩ ብረቶችን ማምረት ላይ ለመስማራት በመፈለጉ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለዚህ ወሳኝ የሆነው ድንጋይ ከሰል ስለሆነና ያለሱ ምንም መሥራት ስለማይቻል ነው ብለዋል።

በሀገራችን ያለው የድንጋይ ከሰል መረጃ በቅርቡ ያለውን የሚያሳይ እንደሆነ የሚጠቁሙት አቶ ቴዎድሮስ፤ የድንጋይ ከሰል ባሕርያት ጥልቅ መሆናቸውን ይናገራሉ። ለዚህም ድርጅቱ ከህንድ፣ ከደቡብ አፍሪካና ከተለያዩ ሀገራት ባለሙያዎችን በማስመጣት በድንጋይ ከሰል ክምችት ዙሪያ ጥናት ማካሄዱንም ይገልጻሉ። በተደረገው ጥናት መሠረትም በኢትዮጵያ ያለው የድንጋይ ከሰል የማቃጠል አቅም ብረትን ለማቅለጥ ከፍተኛ አቅም ያለው መሆኑ መታወቁንም ተናግረዋል።

ይህ የድንጋይ ከሰል ከተመረተ በኋላ እላይ ያሉትን የተለያዩ ኬሚካሎች በመቀነስ ኃይል መጨመር እንደሚቻል አስታውቀዋል፤ የድንጋይ ከሰል ከተመረተ በኋላ በማጠብ የማቃጠል ኃይሉ ከፍተኛ የሆነ የድንጋይ ከሰል ማግኘት እንደሚቻል አመልክተው፣ ወደ ድንጋይ ከሰል ማጠብ ሥራው የተገባውም ለእዚህ መሆኑን ገልጸዋል።

«ፋብሪካው የታጠበ የድንጋይ ከሰል አምርቶ ለፋብሪካዎች ማቅረብ መቻሉ ድርጅቱ በቀጣይ ኢንቨስት አደርግበታለሁ ብሎ ወደያዘው ብረት የማምረት ትልቅ ኢንቨስትመንት ለመግባት የሚያስችለውን ሥራ ከወዲሁ እንደጀመረ የሚያሳይ ነው» ብለዋል፤ አሁን የታጠበ የድንጋይ ከሰል ምርቱን በዋነኝነት ተጠቃሚ ለሆኑት የሲሚንቶ ፋብሪካዎች እያቀረበ እንደሆነም ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ፋብሪካው በተገነባበት በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከማሼ አካባቢ በርካታ የድንጋይ ከሰል ክምችት መኖሩ ተረጋግጧል፤ ከዚህ ክልል አዋሳኝ በሆነው የኦሮሚያ ክልል በወለጋ አካባቢም እንዲሁ ብዙ ክምችት አለ። በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል በተደረገ አሰሳ 50 ሚሊዮን ቶን የሚሆን የድንጋይ ከሰል ክምችት እንዳለ ለማወቅ ተችሏል።

ከማዕድን ሚኒስቴር የተገኘን መረጃ ዋቢ አድርገው አቶ ቴዎድሮስ እንደተናገሩት፤ የድንጋይ ከሰል ከውጭ ለማስገባት ከ200 እስከ 300 ሚሊዮን ዶላር ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ ከፍተኛ ወጪ ነው። ፋብሪካው ኢትዮጵያ ከሚያስፈልጋት የታጠበ የድንጋይ ከሰል 50 በመቶ ያህሉን ለማሟላት እየሰራ ይገኛል። ሀገር ሰላም ከሆነች ይህንን ብቻ ሳይሆን፣ በርካታ እቅዶችን ማሳካት ይቻላል ብለዋል።

ዳይሬክተሩ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ዓይነት የድንጋይ ከሰል አለ፤ በኢትዮጵያ «ሰብ ቢትመስ» እና «ቢትመስ» የሚባሉት የድንጋይ ከሰሎች በብዛት ይገኛሉ። «ቢትመስ» የተሰኘው የድንጋይ ከሰል ዓይነት የማቃጠል አቅም 5ሺ ካሎሪ ወይም ቢበዛ ደግሞ ከ6ሺ ካሎሪ አይበልጥም። ከውጭ የሚገባው «አንትራሳይት» የሚባለው የድንጋይ ከሰል ዓይነት የማቃጠል አቅሙ ከፍተኛው ከ7ሺ ካሎሪ በላይ የሆነ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ከ5ሺ ካሎሪ በላይ የማቃጠል አቅም ያለው የድንጋይ ከሰል የሚጠቀም ኢንዱስትሪ እንደሌለም ጠቅሰው፣ 7ሺና ከዚያ በላይ ካሎሪ የማቃጠል አቅም ያለው የድንጋይ ከሰል የሚጠቀመው ኢንዱስትሪ በጣም ግዙፍ ኢንዱስትሪ መሆኑን ገልጸዋል። በዚህም ደረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ የተዋቀረ ኢንዱስትሪ የለም ይላሉ።

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ኃይል የሚፈልጉት ሴራሚክና ሲሚንቶ አምራች ፋብሪካዎች መሆናቸውን ጠቅሰው፣ እነርሱም ከ5ሺ በላይ ካሎሪ የማቃጠል አቅም ያለው የድንጋይ ከሰል እንደማይፈልጉም ተናግረዋል። ፋብሪካውም ይህንን ኃይል በሀገር ውስጥ በማምረት ለፋብሪካዎች እያቀረበ ይገኛል ብለዋል።


ፎቶ ፋይል

**የድንጋይ ከሰል ከውጭ ለማስገባት ከ200 እስከ 300 ሚሊዮን ዶላር ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ ከፍተኛ ወጪ ነው። ፋብሪካው ኢትዮጵያ ከሚያስፈልጋት የታጠበ የድንጋይ ከሰል 50 በመቶ ያህሉን ለማሟላት እየሰራ ይገኛል**

ፋብሪካው የታጠበ የድንጋይ ከሰል ምርቶች እያመረተ ለገበያ እያቀረበ ቢሆንም የገበያ ትስስሩ ከጸጥታ ጋር የተያያዙ ችግሮች እያጋጠሙት መሆናቸውንም አቶ ቴዎድሮስ ጠቁመዋል፤ ድርጅቱ ምርቶቹን ለፋብሪካዎች ለማድረስ ባሉት የትራንስፖርት አማራጮች በመጠቀም ጥረት እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ ሌላ ተጨማሪ የጭነት አገልግሎት የሚሰጡ ትራንስፖርት አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉም ገልጸዋል።

ይህንን የጭነት አገልግሎት የሚሰጡ የትራንስፖርት አቅራቢዎች ፋብሪካው ባለበት አካባቢ ለመድረስ የጸጥታ ጉዳይ ስጋት ሆኖባቸው መቆየቱን አቶ ቴዎድሮስ ጠቅሰዋል። እንዲያም ሆኖ ችግሩን በመጋፈጥ ለመሥራት የሚፈለጉትም ከገበያ ዋጋ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የትራንስፖርት ታሪፍ እንደሚጠይቁ አመልክተዋል። ይህ ችግር ምርቱ በሚፈለገው ጊዜና በወቅቱ ለደንበኞች ለማቅረብ እንቅፋት መሆኑን ጠቅሰው፤ እስካሁን ድርጅቱ ብዙ ችግሮችን ችሎ ገበያውን ለማርካት ብቻ እየሰራ እንደሆነም ይናገራሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ከተወሰኑ ፋብሪካዎች ጋር ባለው የውል ስምምነት መሠረትም ምርቶቹን እያቀረበ ነው። ፋብሪካው ባለፈው ዓመት ደንበኞቹ ሀገር ውስጥ በሚመረተው የታጠበ የድንጋይ ከሰል ምርት ያላቸው እርካታ ምን ያህል እንደሆነ ለማረጋገጥ ይሰራል። አሁን እየተገነቡ ካሉ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ጋርም ኮንትራት በመግባት ምርቶቹን ለማቅረብ እየሰራ ነው።

ፋብሪካው ለበርካታ ዜጎች የሥራ እድል መፍጠሩንም ጠቅሰው፣ 250 ቋሚ ሠራተኞች እንዳሉትም ጠቁመዋል። በማህበር ተደራጅተው ከድርጅቱ ጋር ለሚሰሩ 700 ተጨማሪ ዜጎችም ጊዜያዊ የሥራ እድል መፈጠር ችሏል ብለዋል።

በዘርፉ ልማት በጣም የላቁ የሚባሉ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እንዳሉም ጠቅሰው፣ እነዚህን ቴክኖሎጂዎች ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት እጅግ በጣም ጥራቱን የጠበቀ የድንጋይ ከሰል በማምረት ለደንበኞች ለማቅረብ ድርጅቱ በትኩረት እየሰራ መሆኑንም አቶ ቴዎድሮስ ጠቁመዋል። አዲስ ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት እንደሚጠይቅ ተናግረው፣ ይህን እቅዱን ለማሳካት ከመንግሥት ድጋፍ በመጠየቅ ከልማት ባንክ ብድር ለማግኘት በሚያስችል ሂደት ላይ እንደሚገኝም ተናግረዋል። ይህ እውን ከሆነ ኢትዮጵያ በማዕድን ዘርፉ በተለይ በድንጋይ ከሰል ልማት በአጭር ጊዜ ውስጥ አሁን ካለችበት ደረጃ መላቀቅ እንደምትችልም ገልጸዋል።

አቶ ቴዎድሮስ እንደተናገሩት፤ በኢትዮጵያ ያለው የድንጋይ ከሰል ክምችት በብዛቱ ብቻ ሳይሆን በአቀማመጡና ሂደቱ ከሌሎች ሀገራት ይለያል፤ በተለይ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ እና በቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል የሚገኘው የድንጋይ ከሰል ውፍረቱ በራሱ ልዩ ነው።

አሁን በማዕድን ዘርፉ ከተሰማሩት አብዛኞቹ ባሕላዊ የማዕድን አማራቾች መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የዘርፉ ልማት ከባህላዊ አሰራር ወጥቶ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን ለማድረግ በማዕድን ልማት ላይ በትኩረት መሥራት እንደሚጠበቅ አመላክተዋል። ይህንን በመቀየር ትኩረት ተሰጥቶ ከተሰራ በሀገሪቷ ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ እምርታ ማምጣት ይቻላል ብለዋል።

ኢትዮጵያ ውስጥ የድንጋይ ከሰል በማውጣት ሂደቱ ላይ ከፍተኛ የእውቀት ክፍተቶች እንዳሉም አቶ ቴዎድሮስ ጠቁመዋል፤ በመንግሥት በኩል በተለያዩ ዘዴዎች የእውቀት ክፍተቶችን ለመሙላት ጥረት መደረግ እንዳለበት ተናግረው፣ ይህ ካልሆነ የምርት ብክነት እንደሚከሰት፣ ትርፋማና ውጤታማ ሥራ ለመሥራት እንደማይቻልና አቅራቢዎችም እንዲዳከሙ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ነው ያመለከቱት። ችግሩ ዘርፉን ለማዘመን የሚደረገውን ሂደትም አዳጋች ያደርገዋል ነው ያሉት። የድንጋይ ከሰል ሥራ የድንጋይ ከሰል ፈቃድ ከመስጠት ጀምሮ ማዕድኑ እስከ ማውጣት ሂደት እና የመሳሰሉት እያንዳንዳቸው ሂደቶች በእውቀት መመራት እንዳለባቸውም አስገንዝበዋል።

«አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅመን የሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል ፍላጎትን አሟልተን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ትኩረት አድርገን መሥራት አለብን» ያሉት አቶ ቴዎድሮስ፣ የድንጋይ ከሰል አቅርቦትን በተመለከተ ያሉት የእውቀት ክፍተቶች ፣ ማዕድን የሚወጣበት መንገድ፣ በክልሎች በኩል ያለው የማዕድን ማውጫ መሬት አቅርቦት እና የጸጥታ ችግሮች ከተስተካከሉ የድንጋይ ከሰሉን በጥሩ ሁኔታ ማምረት ይቻላል» ብለዋል።

በአጠቃላይ በማዕድን ዘርፉ ላይ በመንግሥት በኩል የእውቀት ሽግግር ሥራዎች መሥራት እንዳለባቸው፣ ቴክኖሎጂን መጠቀም እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፣ በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶች ቁርጠኝነት ወሳኝ መሆኑንም አመልክተዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## የስሜት ትኩሳት

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

በሆስፒታሉ የድንገተኛ ክፍል ውስጥ አንድ አባት ሰመመን ውስጥ ወድቀዋል። አጠገባቸው ነጭ የሙያ ልብስ የለበሰች ጠይም ሴት በትካዜ ትታያለች። ከሽማግሌው ወደ እሷ የሚፈስ የሃሳብ ውቅያኖስ በመካከላቸው ተንጣሏል። ፊቷ ላይ በትላንቷ ውስጥ የረቀቀ እውነት ይታወሳታል..በዛሬዋ ውስጥ የወገገ አሁን..በነገዋ ውስጥም ከሁሉ የተባረከች አንድ ነፍስ ትመጣባታለች። ይሄን መባረክ የሰጣት እሱ ነው... ድንገተኛ ክፍል ውስጥ የተኛው ሽማግሌ።

ጠዋት ከእንቅልፏ ስትነሳ ማለዳዋን የምትጀምረው የእሱን ድምጽ በመስማት ነበር። የኔ ቆንጆ ነቃሽ? ጣፋጭ ቁርስ ሰርቼልሻለው፣ ፊትሽን ታጥበሽ ጠብቂኝ› ብሏት ከአልጋው ላይ ወርዶ ወደ ማዕድ ቤት ሲሄድ አልጋ ላይ ሆና ታየዋለች። ዛሬም ድረስ ያልበላችውን ጣፋጭ ቁርስ እያጎረሰ ያበላታል። በጣም የሚገርመው ደግሞ እሷን ከማጉረስ በቀር አንዴም አለመጉረሱ ነበር። ስሟት..አቅፏት.. እንደሚወዳት ሚሊየን ጊዜ ነግሯት ወደ ትምህርት ቤት ይሸኛታል። ሆስፒታሉ ጀርባ የተማሪዎቹ ሰርቪስ ከዓይኑ እስኪሰወር ድረስ ቆሞ ያያታል..። ከጠዋት እስከ ማታ ድረስ ያለው ጊዜ ለነዚህ ርሀብተኛ ነፍሶች የዝንተ ዓለም ያክል ሩቅ ነበሩ። በእሷ ትንሽዬ ነፍስ ውስጥ የአባቷ ገናና ነፍስ የእግዜርን ያክል ጉልበት ነበራት። በልጅነቷ እግዜርን አታውቀውም.. እግዜር የእሷ አባት ነበር የሚመስላት። በእሱ ገናና ነፍስ ውስጥ የእሷ ትንሽዬ ነፍስ ሰፊ የፍቅር ግዛት ነበራት። ይገርመዋል አባትነት..ይገርመዋል ወንድነት..ይገርመዋል ተፈጥሮ። በትንሽ ነፍስ ትልቅ ነፍሱ አቅም ማጣቷ ይገርመዋል። በትላንት በዛሬና በነገው ውስጥ ያለ ያልተመለሰ አምላካዊ ሚስጢር ይለዋል..የፍቅርን ኃይል።

ማታ ሲሆን በቆመበት ቦታ ሆኖ ይቀበላታል። ገና ስታየው በልጅነቷ ውስጥ ይሄ ነው የማትለው ስሜት ይለኮሳል። የጓደኞቿን ስንብት ችላ ብላ፣ የነባሮክና፣ የነአምራን ቻው ቻው ሳይሰማት ወደ አባቷ ትከንፋለች። ከብርሃን ፈጥና፣ ከንፋሳት በና፣ ዓይኖቿን ከአባቷ አካልና ነፍስ ላይ ሳታዛንፍ እጆቿን እንዳንጨፈረረች እቅፉ ውስጥ ትወድቃለች። ያኔ አባቷ እግዜር ይመስላታል። ያኔ ለዘላለም በማይጥሉ ጽኑ ክንዶች የታቀፈች ይመስላታል። ያኔ እንዳባቷ ኃይል የተቀባ ሌላ ነገር ታጣለች። ያኔ አባቷን የዓለም ሁሉ ጌታ ታደርገዋለች። ይሄ ጊዜ አይደለም ቆማ አልፋም የሚታወሳት ይመስላታል። አባቷ በእሷ ሕይወት ውስጥ ሁሉም ቦታ አለ..ያ ጊዜ ግን ከሁሉም የተለየ ነው። ለዘለዓለም የተለያት የሚመስላትን አባቷን እሷን ሲጠብቅ ቆሞ የምታገኘው እዛ ቦታ ነው...ከሆስፒታሉ ጀርባ። ያ ጊዜ በሕይወቷ ውስጥ ዳግም እንዲመጣ የምትሻው የሴትነቷ አልፋ ነው።

እቅፉ ውስጥ እያለች ደጋግሞ ይስማታል። ዓይኗን፣ ጉንጯን፣ ግንባሯን። እቅፉ ውስጥ እያለች ከነቦርሳዋ ተሸክሟት ወደ ቤት ይሄዳሉ። በሆስፒታሉ አጠገብ ሲያልፉ ነጫጭ የለበሱ ሐኪሞችን ማየት ግድ ነበርና እሷም እንዲህ ማለት ግድ ነበረባት..‹አባ እኔ ሳድግ ዶክተር ነው የምሆነው..›

‹ለምን..?

‹አንተን እንዳክምህ...አንተን በሽታ እንዳያምህ› አለችው፡

ሳማት..ነፍሷን በነፍሱ ሳማት። ጉንጬዋ ለአፉ ቅርብ ነበርና ደጋግሞ ሳማት። በዚያ ሰዓት ሊያደርገው የሚችለው የመጨረሻ ውድ ስጦታው እሷን መሳም ነበርና ሳማት። ነፍሱ ውስጥ በቀለች..። እሱ ይሄን ሁሉ ሲሆን እሷ በአባቷ እቅፍ ውስጥ አንገቷን ሰብራ ከሆስፒታሉ ግቢ ወዲያ ወዲህ የሚሉትን ነጭ ለባሽ ዶክተሮች በቅናት እያየች ነበር።

ማታ ሲሆን ሌላ ታሪክ አላቸው...የእሱም የእሷም ነፍስ የሚሹት ልጅነታዊና አባታዊ ታሪክ። ተረት ያነብላታል፣ እየተጫወቱና እያስጠናት ትንሽ ይቆያሉ። ከዛ ሁሉም ነገር በእሷ እንቅልፍ ይጠናቀቃል። ወደመኝታዋ እስክትሄድ ድረስ እሱ ክንድ ላይ ነው እንቅልፍ የሚጥላት። ካለአባቷ ጉያ አንቀላፍታ አታውቅም። ካለአባቷ ክንድ ዓለም ላይ ምቹ ነገር ያለ አይመስላትም። ክንዱ ላይ ተኝታ ጠዋት ክንዱ ላይ ትነቃለች። ፍቅሯ በእንቅልፍ ይሸነፋል። ጠዋት ራሷን ማታ እንደሆነችው ክንዱ ላይ ታገኘዋለች። ከዛም ‹የኔ ቆንጆ ነቃሽ? ጣፋጭ ቁርስ ሰርቼልሻለሁ፣ ፊትሽን ታጥበሽ ጠብቂኝ› ከወፎቹ ዜማ ቀድማ የምትሰማው የአባቷ ድምጽ ይከተላል። በዚያ ማለዳ ከአባቷ ጎን ራሷን እንደማግኘት የሚያስደስታት ምንም አልነበረም። በዚያ ማለዳ ከወፎቹ ድምጽ ልቆ የአባቷን የእንዴት አደርሽ ድምጽ እንደመስማት የሚባርካት ምንም አልነበረም። በዚያ ማለዳ ከአባት የእምነት ጽላት ስር የእሷን የተስፋ ጽላት እንደ ማግኘት ምንም አልነበራትም። አባቷ የሴትነቷ ቀለም ነው። ዓለምን በልኳና በመጠኗ የሰራላት። ከወዙና ከወዟ እያጠቀሰ ያበጃት። ዓለምን የሞሏት የመልካም ወንዶች ነፍስ በመልካም ሴቶች ነፍስ የሰለጠኑ እንደሆኑ ታውቃለች። የአባቷ አሰልጣኝ ማን ትሆን? ሚስቱን ማወቅ ጓጓች..ሚስቱ እናቷ እንደሆነች ስታውቅ ደግሞ በይበልጥ ጓጓች..ክብር የዋጀው ጉጉት። ወደፊት..ወደፊት ብቻ አይደለም ለዘላለም እንደ አባቷ ዓይነት ባል እንዲኖራት ተመኘች። እንደ አባቷ ዓይነት ወንድም፣ እንደ አባቷ ዓይነት ልጅ፣ እንደ አባቷ ዓይነት ጓደኛ እንዲኖራት ተመኘች። ሴቶች ሁሉ፣ ልጆች ሁሉ፣ ሰዎች ሁሉ እንደ አባቷ ዓይነት ወንድ ቢያገኙ ስትል..

መስፍን አባቷ እንደሆነ ያወቀችው ቆይታ ነው.. እናቷም አባቷም እንደሆነ ነበር የምታውቀው። እናትነት ምን እንደሆነ ያወቀችው ትምህርት ከጀመረች በኋላ ነበር። ትምህርት ቤት ጓደኞቿ እናታቸውንና አባታቸውን ይዘው ሲሄዱ እሷ ግን ከአባቷ ጋር ብቻ ነበር የምትታየው። እኚህ ቀናት.. እኚህ አጋጣሚዎች ተደጋገሙና መስፍን አባቷ ብቻ እንደሆነ ነገሯት። አንድም ቀን ግን እማዬስ ብላው አታውቅም። ከፍቅሩ ጢሻ ውስጥ ያጎደለባት አንዲት አለላ ሰበዝ አልነበረችም። ለምን እማዬስ ትበለው? እናት ቢኖራት መስፍን እያደረገላት ካለው ነገር በላይ ምን ታደርግላት ነበር? መልሷ ዛሬም ነገም እስከ ዘላለም ድረስ ምንም የሚል ነው። ልክ እንዳባቷ ነፍስ አንዳንድ ነፍሶች ጥንድ ናቸው። ለዘላለም እንዳይታክቱ ሆነው የተበጁ። ልክ እንዳባቷ ነፍስ አንዳንድ ወንዶች ወንድና ሴት ናቸው። ሳይጎድሉ የሚኖሩ። ልክ እንደ አባቷ ነፍስ የአንዳንድ አባቶች ነፍስ ሰማያዊ ናት..በጸጋ የተሞላች።

አደገች..! በልጅነቷ አባቷ ትከሻ ላይ ሆና ሆስፒታሉ ግቢ ውስጥ እንዳየቻቸው ሐኪሞች ዶክተር ሆነች። አባቷ ደግሞ አጠገቧ ሰመመን ውጦት አንቀላፍቷል...

አባቷን ስታስብ..ስታስብ..ወደእሱ ስትሄድ አይደክማትም...ትበረታለች። በመኖሯ ውስጥ ሌላ መኖር አለ። አምላክ በዚህ ሁሉ ውስጥ አንድ እውነት አለ፤

የፈጣሪ ማስተዋል ይገርማታል። የተፈጥሮ.. ውስጥ ያለው

ከሁሉም በኋላ አንድ መራራ እውነት ላይ ደረሰች..መስፍን አባቷ እንዳይደለ አወቀች...ከመንገድ ላይ አግኝቶ ሊያሳድጋት እንደወሰዳት ነገራት። እሱና ነፍሱ በሕይወቷ ሁሉ ያስደንቋታል።

የልጅነት ጠረኗ አይረሳውም..የአንገቷ ስር ሽታ.. የቀሚሷ አቧራ፣ የመዳፏ ስር እድፍ። እንዳባቷ ዓይነት መልካም ነፍስ ያላቸውን ስታገለግል ግን ትኖራለች። አጠገቧ ድንገተኛ ክፍል ውስጥ ሰመመን የዋጣቸው አዛውንት ዓይናቸውን ገለጡ...

# ዓለም አቀፍ




## አሜሪካ ለ20 ከተሞች የ53 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ለማድረግ ቃል ገባች

በጋዜጣው ሪፖርተር

አሜሪካ በታዳጊ ሀገራት ለሚገኙ 20 ከተሞች የ53 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ለማድረግ ቃል መግባቷን የአሜሪካ የልማት ተራድኦ ድርጅት (ዩኤስአይዲ) ኃላፊ ሳማንታ ፓወር አስታወቁ።

የዩኤስአይዲ ኃላፊ ሳማንታ ፓወር የከተሞቹን የአየር ንብረት ለውጥ ችግር የመቀነስ ጥረታቸውን ለመደገፍ በታዳጊ ሀገራት ለሚገኙ 20 ከተሞች የ53 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ለማድረግ ቃል ገብተዋል።

አሜሪካ በታዳጊ ሀገራት ለሚገኙ 20 ከተሞች የ53 ሚሊዮን ዶላር ድጋፍ ለማድረግ ቃል የገባች ሲሆን፤ ለዓለም የከባቢ አየር ብክለት 75 በመቶ የሚሆነውን ድርሻ የሚይዙት ከተሞች መሆናቸውን ገልጸዋል።

ድጋፉ የከተሞቹን የአየር ንብረት ለውጥ ችግር የመቀነስ ጥረታቸውን ለማገዝ የሚውል ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ እንደ ኤሌክትሪክ መኪና የመሳሰሉ የካርቦን ልቀትን ለሚቀንሱ ፕሮጀክቶች ይውላል ብለዋል።

የኪሪግዝ ዋና ከተማ ቢሽኪክ፣ የህንዷ ራጅኮት፣ የደቡብ አፍሪካዋ ሞምቤላ እና የሜክሲኮዎቹ ሁለት ከተሞች ከርዳታው ተጠቃሚ ከሚሆኑት ከተሞች መካከል ናቸው ተብሏል።

ሳማንታ ፓወር ታዳሽ ያልሆነ የኃይል ምንጭ መጠቀም ይቁም ወይስ አይቁም የሚል ድርድር እየተካሄደ ባለበት የዱባዩ የኮፕ28 ስብሰባ ላይ ተካፍለዋል።

የኮፕ28 ስብሰባ 198 ሀገራት የተወከሉበት ሲሆን ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥ የሚያስከትለውን ችግር ለመቋቋም የሚያስችል እና የሚቴን ጋዝ ልቀትን ለመቀነስ የሚያስችል የገንዘብ ድጋፍ ቃል ገብተዋል።

## አንቶኒዮ ጉቴሬዝ የጸጥታው ምክር ቤት በአፋጣኝ ተሰብስቦ በጋዛ ጉዳይ ውሳኔ እንዲሰጥ አሳሰቡ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የተባበሩት መንግሥታቱ ድርጅት (ተመድ) ዋና ፀሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ የተመድ ጸጥታው ምክር ቤት በአፋጣኝ ተሰብስቦ በጋዛ ጉዳይ የተኩስ አቁም ውሳኔ እንዲሰጥ አሳሰቡ።

በተመድ ማቋቋሚያ ቻርተር አንቀጽ 99 ላይ ዋና ፀሐፊው ዓለም አቀፍ የሰላምና ደህንነት ስጋት ተደቅኗል ብለው ሲያምኑ የጸጥታው ምክር ቤትን የማሳሰብ ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል።

ይህን አንቀጽ በመጠቀም ጉቴሬዝ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ የእስራኤልና ሃማስ ጦርነት እየተባባሰ እንዳይሄድ የትኛውንም ዓይነት ጫና የማድረግ ኃላፊነት አለበት ያሉት ጉቴሬዝ፤ 15 አባላት ላሉት የጸጥታው ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ደብዳቤ አስገብተዋል።

ምክር ቤቱ በአፋጣኝ ተሰብስቦ በጋዛ እየተባባሰ የመጣውን ሰብዓዊ ቀውስ የሚገታ ውሳኔ እንዲያሳልፍም ነው ያሳሰቡት።

የተመድ ቃል አቀባይ ስቴፋን ዱጃሪክ፤ ዋና ፀሐፊው በዚህ ሳምንት በጸጥታው ምክር ቤት ስብሰባ ተገኝተው ምክር ቤቱ ሁለት ወራት ለደፈነው ጦርነት አስቸኳይ ውሳኔ እንዲሰጥ ጥሪ ያቀርባሉ ብለዋል።

የጉቴሬዝን የማሳሰቢያ ደብዳቤ ተከትሎም የጸጥታው ምክር ቤት አባል የሆነችው አረብ ኤምሬትስ በጋዛ የሰብዓዊ ተኩስ አቁም እንዲደረስ ረቂቅ የውሳኔ ሃሳብ ለምክር ቤቱ ማስገባቷን ገልጻለች።

በጸጥታው ምክር ቤት ከዚህ ቀደም የቀረቡ የተኩስ አቁም የውሳኔ ሃሳቦች ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት ባላት አሜሪካ ውድቅ መደረጋቸው የሚታወስ ነው።

ዋሽንግተን የተኩስ አቁም የውሳኔ ሃሳቡ የፍልስጤሙን ሃማስ የመዘጋጃ እድሜ ይጨምርለታል በሚል ነው የውሳኔ ሃሳቦቹን የተቃወመችው።

ምክር ቤቱ የተመድ ዋና ፀሐፊው በአንቀጽ 99




የተሰጣቸውን ሥልጣን ተጠቅመው ያቀረቡትን የተኩስ አቁም ውሳኔ ይደረስ ሃሳብ ተቀብሎት ከጸደቀ በጦርነቱ ተሳታፊዎች ላይ ማዕቀብ የመጣልና የውጭ ሀገር ወታደሮችን እስከ ማስገባት የደረሰ ርምጃ መውሰድ ይችላል።

አሜሪካ ግን ድጋፍ ትሰጠዋለች ተብሎ አይጠበቅም ብሏል አሶሼትድ ፕረስ በዘገባው።

በመንግሥታቱ ድርጅት የእስራኤል አምባሳደር ጊላድ ኢርዳንም የጉቴሬዝን ርምጃ “ከሞራል ዝቅ ያለ እና ከእስራኤል በተጻራሪ የቆመ” ሲሉ ተቃውመውታል።

የዋና ፀሐፊው የተኩስ አቁም ጥሪ ሃማስ በጋዛ የሽብር ተግባሩን እንዲቀጥል እንደመፈለግ የሚታይ ነው ሲሉም ጉቴሬዝን ወቅሰዋል።

የመንግሥታቱ ድርጅት ዋና ፀሐፊ አንቶኒዮ ጉቴሬዝ ከጥቅምት 18/ 2023 ጀምሮ በጋዛ ተኩስ እንዲቆም እያቀረቡት የሚገኙት ጥሪ ከእስራኤል መንግሥት ተደጋጋሚ ትችት እንዳስከተለባቸው አል አይን ዘግቧል።

# የሀገራችን ትንሳኤ የእኛ ትንሳኤ ነው

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ሀገራችን ኢትዮጵያ መልከ ብዙ የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እናት ናት። ብዙ ልጆችን፣ ብዙ መልኮችን፣ ብዙ ወግና ልማዶችን፣ ብዙ ሥርዓትና ባሕሎችን ታቅፋ የያዘች ናት። የእናት ሆድ ዥንጉርጉር እንደሚባለው ቁርጥ እሷን መሳይ እልፍ መልከኛ ልጆችን ታቅፋለች። ይሄ የእናት ጉያ..ይሄ የእምዬ እቅፍ ልዩነት የለውም። በተለያዩ ብሔሮች፣ በተለያዩ ቋንቋዎች፣ በተለያዩ ባሕሎችና ሥርዓቶች የቆነጀ የእናት ዓለም ክንድ ነው። በተለያዩ መልኮች፣ በተለያዩ ቀለሞች፣ በተለያዩ ዘዬዎች የበረታ የእናት ዓለም ጉያ ነው።

ሀገራችን ኢትዮጵያ ልጆቿን ለመታቀፍ፣ ልጆቿን ለመሰብሰብ ታክታ አታውቅም። ቢዘረጋ ከዚህ እስከዛ የሚደርስ የርህራሄና የደግነት፣ የታሪክና የሥልጣኔ ክንድ አላት። እኛ እንዋደድ፣ ልዩነታችንን ለውበት፤ ውበታችንን ለአንድነት እንጠቀመው እንጂ የኢትዮጵያ መዳፍ ሰፊ ነው። እኛ ፍቅርን እንወቅ፣ በምክክርና በንግግር ችግሮቻችንን እንፍታ እንጂ፤ ጉያዋ ለብዙዎች የሚበቃ ነው። እኛ በአንድ ሀሳብ፣ በአንድ ልብ እንቁም እንጂ ቤቷ..ሳሎኗ ሙሉ ነው።

ለየትኛውም ሀገርና ሕዝብ ብዙኃነት በረከት እንጂ መርገምት የለውም። አሁናዊ የልዩነት ትርክቶቻችን ብዙኃነት የፈጠራቸው ሳይሆኑ ጥቂቶች ለራሳቸው ፍላጎት የፈጠሩዋቸው ናቸው። ቁጭ ብሎ ለመነጋገር ፈቃደኛ ባልሆኑ አካላት ያመጣብን ጣጣ ነው። የትኛውም ቀዳዳ በምክክር የሚደፈን ነው። የትኛውም አባጣና ጎርባጣ በመተሳሰብ የሚቀና ነው።

ተስፋ የአንድነት ቀለም ነው። የኢትዮጵያ ተስፋ የእኛ አንድነት ነው። የሀገራችን ቀና ማለት የእኛ ወንድማማችነት ነው። ያለን ነገር ከኢትዮጵያዊነታችን አይበልጥም። ለልጆቻችን ልናወርሳቸው የምንችለው ትልቁ የሰውነት ውርስ በብዙኃነት ውስጥ አብሮነትን የማስቀጠል ጥበብን ነው። ፍቅርን አግነን፣ አብሮነትን አስበልጠን እንደ አብረሃምና ሎጥ እኛ ወንድማማቾች ነን ልንባባል ይገባል። በዚህ ሀሳብ እና እውነት ውስጥ ነው ዋጋና ክብር የሚኖረን።

ሰው በሀገር ሲጠራና ሀገር በሰው ስትጠራ አንድ አይነት አይደለም። ሰው በሀገር ሲጠራ እዛ ጋ ሙሉ መሆን ይጀምራል። ሰው ስሙን፣ እምነቱን፣ ክብሩን፣ ማንነቱን ሀገሩ ሲያደርግ ሥልጣኔና ዘመናዊነት ዋጅተውታል እንላለን። ሰው በሀገሩ ሲጠራ የዜግነት ግዴታውን እየተወጣ ነው። ሀገር በሰው ስትጠራ ግን ብዙ ጊዜ ልክ አይመጣም። ብሔራችንን ታከን፣ የብቻ ታሪካችንን ተንተርሰን ሀገራችንን በእኛ ስንጠራ እዛጋ ስህተት እየሠራን ነው። በመሠረቱ ሰው በሀገር እንጂ ሀገር በሰው ተጠርታ አታውቅም። እናም መጠሪያ ስማችንን ከእኔነት ወደእኛነት፣ ወደብዙኃነት በመቀየር የኅብረብሔራዊነት እድላችንን ወደ ድል መቀየር እንችላለን።

ብዙ መልክ አንድ ስም የኢትዮጵዊነት የታሪክ መነሻ ነው። ብዙ ነን..ሰማኒያ እና ከዛ በላይ። የተትረፈረፍን..ይሄ ሁሉ የሀሳብና የኑባሬ ውሕደት በሀገርና ሕዝብ ላይ የሚንጸባረቅ ነው። መልካም ሀሳብ መልካም ታሪክ መፍጠሪያ ነው። ለፍቅር እንጂ ለጠብ መቧደን አያምርብንም። በፍቅር ስም ለአንድነት በአንድነት ተቧድነን የጋራ ታሪክ ጽፈን ፊተኞች ተብለናል። ያን ደማቅ እድልና ድል ለመመለስ ለጥላቻ የተዘረጉ እጆቻችን፣ ለጠብ ያሞጠሞጡ አፎቻችን ፍቅርን መስበክ አለባቸው።

አንዳንዶቻችን በሀገራችን የምንጠራ ነን አንዳንዶቻችን ደግሞ ሀገራችንን በማንነታችን የምንጠራ ነን። የሚልቀው እውነት ሰው በሀገሩ ሲጠራ የሚለው እውነት ነው። ከሀገር የቀደመ ነገር ሁሉ የውድቀት ምንጭ ነው። ከሕዝብ የበረታ ነገር ሁሉ መድረሻው ምንምነት ነው። ሀገር የሚያቆመው፣ አንድነት የሚፈጥረው ከሀገር ያልቀደመው ነገር ነው። እርሱ የሥልጣኔ መጀመሪያ ነው። ከሀገር የቀደመ ነገር እንዳይኖረን እንጠንቀቅ ።

ሰው ራሱንም ሆነ ብሔሩን፣ ታሪኩንም ሆነ ማንነቱን ከሀገሩ ሲያስቀድም ያኔ ባለውለታነቱ ያበቃል። ኢትዮጵያ ሀገራችን እስከዛሬ ድረስ በሥልጣኔና በታሪክ፣ በባሕልና በወንድማማችነት ከፍ ብላ የታየችው ሀገራቸውን ባስቀደሙ ብሔር ብሔረሰቦች ነው። ዛሬም ካሉብን ወደፊትም ከሚኖሩብን ሀገራዊ ትርክቶችና ተረት ወለድ ጥላቻዎች እንላቀቅ ዘንድ ሀገሩን ያስቀደመ፣ ወገኑን ከፊት ያደረገ ፖለቲካና ፖለቲከኛ ያስፈልገናል።

ብዙ ነን..ከራሳችን አልፈን ለሌሎች የምንተርፍ። ብዙ ነን ጥበብን፣ ታሪክን፣ ጀግንነትን አጣምረን የያዝን። ልዩነታችን ውስጥ ብዙ የአንድነት መንፈስ፣ ብዙ የኅብረብሔራዊነት ጌጦች አሉ። ልዩነታችን ውስጥ ሀገር የሚያሻግር፣ ትውልድ የሚቀርጽ የታሪክና የሥርዓት ጀብደኝነት አለ። ብዙኃነታችን ውስጥ እኛነትን የሚያወሳ፣ ግለኝነትን የሚኮንን የሥርዓትና የጨዋነት ልማድ አለ። እኛ ዝም ብለን ሀገርና ሕዝብ አልሆንም። ሌሎችን ባቀናና ባነቃ ባሕልና ሥርዓት እሴትና ልማድ ውስጥ ሀገርና ሕዝብ የሆንን ነን።

በልዩነታችን ብናጌጥ፣ በብዙኃነታችን ብንቆም ዓለምን የሚያስፈራ የኃይልና የለውጥ ባለቤቶች እንሆን ነበር። በወንድማማችነት ብንሰለፍ እንደጥንቱ ዘመን ከራሳችን አልፈን ለሌሎች ብርሃን መሆን የምንችል ነበርን። ለመበርታት በፍቅርና በአብሮነት ለመቆም ያሉንን ግን ደግሞ መለስ ብለን ያላየናቸውንና ዋጋ ያልሰጠናቸውን ፀጋዎቻችንን መጠቀም አለብን። በእኔነት ያደበዘዝናቸውን የወንድማማችነት እሴቶቻችንን የመጪው ዘመን የትንሳኤ ማብሰሪያ እንዲሆኑን እንግለጣቸው።

ሀገር መቼም አንድ ዓይነት ሆና አታውቅም.. የዓለም ታሪክ በመለያየት ውስጥ፣ በመደባለቅ ውስጥ የቆመ ነው። አንድ ዓይነት ብሔር፣ አንድ ዓይነት ባሕል፣ አንድ ዓይነት ቋንቋ፣ አንድ ዓይነት ታሪክና ሥርዓት ያላት ሀገር የለችም። ሁሉም የዓለም ሀገራት በድብልቅልቅ ብሔርና ቋንቋ፣ በልዩ ልዩ ባሕልና ወግ የተሰባጠረ ነው። ውበት ማለት በልዩ ልዩ ባሕሎች መድመቅ ነው። ሥልጣኔ ማለት የብዙኃነትን ሀሳብና ፍላጎት በሠለጠነ መንገድ ማራመድ ነው። ዘመናዊነት ማለት በዚህ ልዩ ልዩ ባሕልና ወግ መድመቅና መዋብ ነው።

ልዩነት ጌጥ ነው። ብዙ ሀገራት አሁናዊ ሥልጣኔያቸውን፣ አሁናዊ ልዕለ ኃያልነታቸውን ያገኙት ኅብረብሔራዊነታቸውን ተጠቅመው ነው። መጠኑ ይለያይ እንጂ ሁሉም ሀገራት በኅብረ ብሔራዊነት ስብጥር ውስጥ የቆሙ ናቸው። ተፈጥሮ ብዙኃነትን ካደለቻቸው ጥቂት ሀገራት መካከል ደግሞ በዋናነት እኛ ኢትዮጵያውያን እንጠቀሳለን። ልዩነት ውበት ነው..በልዩ ልዩ ባሕልና ወግ፣ ሥርዓትና ታሪክ መከበብ መታደል ነው። ይሄን ተፈጥሮ ያደለንን የብዙኃነት ልዩነታችንን በአግባቡ በመጠቀም ሀገራችንን ማሻገር ይኖርብናል።

ለነውጥ ሳይሆን ለለውጥ፣ ለመገፋፋት ሳይሆን ለመተቃቀፍ ልንጠቀመው ግድ ይለናል። ለመለያየት ሳይሆን ለአንድነት፣ ለመራራቅ ሳይሆን ለመቀራረብ ልናውለው ይገባል። ልዩነት ከተጠቀምንበት ለውጥ ካልተጠቀምንበት ነውጥ ነው። ከተጠቀምንበት ወደሥልጣኔና ወደ ከፍታ ልንወጣጣበት እንችላለን። ካልተጠቀምንበት ደግሞ በልዩነታችን ቀዳዳ ውስጥ አፍራሽ አስተሳሰቦችን እያስገባን ልንበላላበት እንችላለን። መቼም የትም ልዩነት ጉድለት ሆኖ አያውቅም። ልዩነት ጌጥ ነው..ሀገር የምታምርበት፣ ትውልድ የሚቆነጅበት፣ ታሪክ የሚያብብበት ስፍራ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ሲበረበር አንድ ዓይነት ግን ደግሞ ልዩ ውበትና ደም ግባት ይገኝበታል። ውበታችን በልዩነታችን ውስጥ ያካበትነው ባሕል፣ ልማድ፣ ወግና ሥርዓታችን ነው። ውበታችን በልዩነታችን ውስጥ ያገኘነው ፍቅርና መከባበር፣ መዋደድና መቻቻላችን ነው። ውበታችን በልዩነታችን ውስጥ የተወራረስነው የአብሮነት መንፈስ ነው። ውበታችን በብዙኃነታችን ውስጥ ማግረን ያቆምነው፣ አቁመን ያጸናነው ኢትዮጵያ የሚለው የጋራ ስማችን ነው። አንድ ዓይነት ውበት የለውም። ውበት ያለው በልዩነት ውስጥ ነው።

ዛሬ ላይ በዚህ ልክ ባለታሪክ የሆንነው በልዩ ልዩ ትውፊታችን ነው። ኢትዮጵያ የተሠራችው ከእያንዳንዳችን ባሕልና ወግ፣ ሥርዓትና ታሪክ በተዋጣ ሀሳብ፣ በተዋጣ ጽናት፣ በተዋጣ እውቀት፣ በተዋጣ ገንዘብ ነው። ኢትዮጵያ ሀገራችን በዚህ ልክ የቆነጀችው በእያንዳንዳችን ብዙኃነት ተከባ ነው። መብዛታችን..የተለያየ መሆናችን የተለየችውን ሀገራችንን ፈጥሯታል። እናም ልዩነታችን ውበታችን ነው ።

ኢትዮጵያን ካስጌጡ ጌጦች ውስጥ ሌላም ሊጠቀስ የሚችል እውነት አለ እርሱም አንድነታችን ነው። ከብዙኃነታችን ውስጥ በተወለደ አንድነታችን ከትላንት እስከዛሬ ብዙ ድሎች በጋራ አጣጥመናል። በልዩነታችን ውስጥ በተዋጡ የአብሮነት መንፈሶች ብዙ ተግዳሮቶችን በጋራ አልፈናል። አሁንም በልዩነታችን ውስጥ ያለውን አንድነታችንን ለሀገር ክብር የምናውልበት ትክክለኛ ጊዜ ላይ ነን። ሀገራችን ኢትዮጵያ ከፊቷ ብዙ ተስፋዎች አሏት። እነኚህ ተስፋዎቿ እውን እንዲሆኑ የእኛ በአንድነት መቆም ዋጋ አለው።

የሀገራችን ትንሳኤ እንዲመጣ፣ ጨለማዋ እንዲነጋ ሰላም ያለበት፣ ምክክር ያለበት፣ ፍቅር ያለበት፣ አንድነት ያለበት፣ ፈሪሐ እግዚአብሔር ያለበት አብሮነት ያስፈልገናል። ሀገር በዜጎቿ የምትሠራ ናት። እኛ ደግሞ ሀገር ለመሥራት የሚሆን ብዙ ጥበብ ብዙ ማስተዋል ያለን ሕዝቦች ነን። እጆቻችን ከእኛ ርቀው ለመላው ጥቁር ሕዝብ ባለውለታ ናቸው። በአንድነት ከቆምን፣ ልዩነቶቻችንን አቻችለን መጓዝ ከቻልን የተሻለች ኢትዮጵያ ለመሥራት በቂዎች ነን።

በብሔር የተለያየን ነን፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በባሕል የተለያየን ነን። ይሄ ሁሉ ልዩነታችን ግን ኢትዮጵያ በሚል የጋራ መጠሪያ ታስሯል። ያማርነው ስለተለያየን ነው..ኢትዮጵያ በሚል የጋራ ስም የታሰርነው ልዩዎች ስለሆንን ነው። በተፈጥሮ እውነት በብዙ ልዩነት ውስጥ አንድ ነን። በብዙ አንድነት ውስጥ ልዩ ነን።

በድብልቅ ውሕደት ኢትዮጵያዊ ተብለናል። ሀገራችን ኢትዮጵያ ብዙ ፍልጥ የታሰረባት ገመድ ናት። ልጡ በአንድ ላይ አስሮናል። ልጡ ቢፈታ ፍልጡ ይበታተናል። ልጡ ቢላላ ፍልጡ ይመሳቀላል። በኢትዮጵያዊነት ስምና ገመድ ነው እንዳንበታተን ሆነን የታሰርነው። ኢትዮጵያዊነት እንዲህ ነው..በልዩነት ውስጥ ጸንቶ የቆመ፣ በልዩነት ውስጥ ጠብቆ የተገመደ..ማንም የማያላላው ሥጋና ደም። የታሰርንበት የአንድነት ልጥ፣ የታሰርንበት የወንድማማችነት ገመድ እንዳይፈታ ልዩነታችንን ማክበር መቻል ይኖርብናል። የታሰርንበት የኢትዮጵያዊነት ገመድ፣ የተያዝንበት የመቻቻል ልጥ እንዳይላላ ልዩነታችንን እንደውበት አምነን መቀበል ይኖርብናል።

ብዙኃነት ለሀገር ያለው ሁለንተናዊ ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በብዙ ነገር የተባረክን ሕዝቦች ነን። በእያንዳንዱ ብሔር ውስጥ ለሀገር የሚሆን ብዙ ነገር አለ። ያ ብዙ ነገር የሀገርን ቀዳዳ፣ የማኅበረሰቡን ችግር የመፍታት አቅም አለው። ችግሮቻችን እንዲበልጡን እድል ካልሰጠናቸው በስተቀር አይበልጡንም። በዚህም በዛም የምንሰማቸው ብሔር ተኮር እኩይ አስተሳሰቦች ሀገራዊ ችግር ከመፍጠር ባለፈ ጥቅም ስለሌላቸው ብዙኃነታችንን ለለውጥ መጠቀም ይኖርብናል። ችግር ፈቺ አስተሳሰብ ይዘን የለውጥና የመፍትሔ አካል መሆን እንጂ በልዩነታችን ውስጥ ሰርገን እየገባን በምንፈጥራቸው ጥቃቅን የልዩነት በሽታዎች ወደ ፊት መሄድ አንችልም።

ተስፋዎቻችን በመዳፋችን ውስጥ ነው ያሉት። ከፍታዎቻችን በእያንዳንዳችን ጫንቃ ላይ የተቀመጡ ናቸው። ሕዝቦቿ በጋራ ያልቆሙባት ሀገር ታሪክ አይኖራትም። ታሪክ የሚፈጠረው ከአንድነት አብራክ ውስጥ ነው። የዓድዋ ታሪክ የመላው ኢትዮጵያዊ ታሪክ ነው። የዓድዋ ታሪክ የብሔር ብሔረሰብ ታሪክ ነው። የህዳሴ ግድባችን ብሔር ብሔረሰቦች በአንድነት ያቆሙት የጋራ ታሪካቸው ነው።

ልዩነታችን እንድንደምቅበት የተሰጠን እንጂ እንድንደበዝዝ የተሰጠን እንዳይደለ በማመን ለአንድ ዓላማ በአንድ እንቁም። ባለን አቅም ሁሉ በአንድ አቅፋ ለያዘችን ለድሀዋ ሀገራችን የምንለፋበት፣ የምንደክምበት ጊዜ ላይ ነን። የሚጠቅመን ፍቅርና አብሮነት ብቻ ነው።

ሀገራችንን የጋራ መጠሪያችን አድርገን ለትንሳኤዋ ብርሃን መሆን ይጠበቅብናል። የሀገራችን ትንሳኤ የእኛ ትንሳኤ ነው..ትንሳኤዋ እውን የሚሆነው ደግሞ በእኛ አብሮነት ነው። አብሮነታችን ኃይላችን ነው። ኃይላችን ደግሞ ከድህነት መውጫችን ነው። በልዩነታችን ተውበን፣ በብዙኃነታችን ደምቀን የሀገራችንን ትንሳኤ እውን እናድርግ ።

> ልዩነታችን ውስጥ ብዙ የአንድነት መንፈስ፣ ብዙ የኅብረብሔራዊነት ጌጦች አሉ። ልዩነታችን ውስጥ ሀገር የሚያሻግር፣ ትውልድ የሚቀርጽ የታሪክና የሥርዓት ጀብደኝነት አለ። ብዙኃነታችን ውስጥ እኛነትን የሚያወሳ፣ ግለኝነትን የሚኮንን የሥርዓትና የጨዋነት ልማድ አለ። እኛ ዝም ብለን ሀገርና ሕዝብ አልሆንም። ሌሎችን ባቀናና ባነቃ ባሕልና ሥርዓት እሴትና ልማድ ውስጥ ሀገርና ሕዝብ የሆንን ነን

# ስፖርት





## የክለቦች የጠረጴዛ ቴኒስ ሻምፒዮና ተጠናቀቀ

ዓስማየሁ ግዛው

የኢትዮጵያ ጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን ያዘጋጀው የክለቦች ሻምፒዮና ትናንት ተጠናቋል። በውድድሩ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክና የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ አጠቃላይ አሸናፊ መሆን ችለዋል። ስምንት ክለቦች በአዋቂና ታዳጊ ስፖርተኞች መሳተፋቸውም ተገልጿል፡፡

ኢትዮጵያ በ2017 ዓ.ም ለምታዘጋጀው የአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ሻምፒዮና ብሔራዊ ቡድኑን የሚወክሉ ተወዳዳሪዎች በሻምፒዮናው እንደተመረጡም የኢትዮጵያ ጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን አስታውቋል። ውድድሩ ከኅዳር 23/2016 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ ላለፉት አምስት ተከታታይ ቀናት ሲካሄድ የነበረ። በዚህም በአዋቂዎች ምድብ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲሁም በታዳጊዎች ምድብ የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ የውድድሩ አጠቃላይ አሸናፊ እና የዋንጫ ተሸላሚ መሆን ችለዋል።

በሻምፒዮናው በሁለቱም ፆታዎች፣ በታዳጊዎችና አዋቂዎች ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታችና ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ተወዳዳሪዎች የተካፈሉ ሲሆን 82 ወንድና 74 ሴት በድምሩ 156 ስፖርተኞች መሳተፋቸው ተጠቅሷል፡፡

በነጠላ በተደረገው ፉክክር ከ18 ዓመት በላይ ወንዶች ኢዮብ ሲሳይ፣ ደራራ መኮንንና መላኩ በላይ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከ1ኛ እስከ ሦስተኛ ያለውን ደረጃ በመያዝ ሲፈጽሙ፤ ከ18 ዓመት በላይ ሴቶች እንዲሁ ሜሮን ከንግድ ባንክ 1ኛ፣ ከና ረዘመ ከኦሮሚያ ፖሊስ 2ኛ እና ዮርዳኖስ ንግዴ ከኢትዮ ኤሌክትሪክ 3ኛ ደረጃን በመያዝ ውድድራቸውን ፈጽመዋል። ከ18 ዓመት በታች ወንዶች ነጠላ ውድድር ቶማስ አስማማው እና ተመስገን ታከለ ከኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ 1ኛ እና 2ኛ ሆነው ሲያጠናቅቁ፣ ዳንኤል ፀጋዬ 3ኛ ደረጃን በመያዝ ጨርሷል። በተመሳሳይ ነጠላ የሴቶች ከ18 ዓመት በታች ውድድር አርሴማ ለማ፣ ታሪኳ አገኘሁ እና ወርቃለም በየነ ከኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ከ1ኛ እስከ 3ኛ ያለውን ደረጃ በመያዝ አጠናቀዋል።



በውድድሩ ስምንት ክለቦች ተሳትፈው ጠንካራ ፉክክር አድርገዋል፣

በአፍሪካ ሻምፒዮና ማሰለፍ የሚፈቀደው አምስት ተጨዋቾች ቢሆንም ኢትዮጵያ አዘጋጅ ሀገር በመሆኗ 7 በነጠላ ወንድ እና 7 በነጠላ ሴት፣ በጥቅሉ 14 ስፖርተኞችን እንደምታሰልፍ ተገልፃል። ለዚህም በውድድሩ የሚሳተፈውን ብሔራዊ ቡድን የሚወክሉ ስፖርተኞች በዚህ ሻምፒዮና እንደተመረጡ ለማወቅ ተችሏል። ለተመረጠው ቡድን ዝግጅት እና መስተንግዶ ኮሚቴ እንደተዋቀረ የተገለጸ ሲሆን ለብሔራዊ ቡድኑ ድጋፎችን በማፈላለግ ጥሩ የሆነ ዝግጅት እንደሚደረግም ታውቋል፡፡

ኢትዮጵያ አዘጋጅ ሀገር እንደመሆኗ የተሻለ ዝግጅትን አድርጋ ለዓለም ጠረጴዛ ቴኒስ ሻምፒዮና የሚያበቃትን ውጤት ለማስመዝገብ ከወዲሁ እየተሠራ እንደሆነም ተጠቁሟል። ኢትዮጵያ በምሥራቅ አፍሪካ ደረጃ ጥሩ ብትሆንም እንደ አፍሪካ ተፎካካሪ ለመሆን ብዙ ሥራዎች መሠራት እንዳለበትም ተጠቅሷል። በመሆኑም የተሻለ ውጤትን ለማስመዝገብና ቀድሞ ለመዘጋጀት ታስቦ የብሔራዊ ቡድኑ ምርጫው ቀደም ብሎ ሊደረግ ችሏል፡፡

የኢትዮጵያ ጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት አቶ ተስፋዬ ብዛ፣ የብሔራዊ ቡድኑን ምርጫ አስመልክቶ ለአዲስ ዘመን እንደገለፁት፣ ኢትዮጵያ በመጪው ዓመት የአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ሻምፒዮናን እና የአፍሪካ ጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን ጠቅላላ ጉባኤን ታስተናግዳለች። ውድድሩ ሀገር ውስጥ ከመካሄዱ አንጻር ለዓለም ሻምፒዮና ማጣሪያ የሚያበቃ ውጤት ለማምጣት ታቅዶ እየተሠራ እንደሆነ ተናግረዋል። ኢትዮጵያ በአፍሪካ ደረጃ ተፎካካሪ ለመሆን ብዙ መሠራት የሚያስፈልግ በመሆኑ ሰፊ ዝግጅት ለማድረግ ታስቦ ብሔራዊ ቡዱን መምረጫ ውድድሩ ቀደም ብሎ ሊከወን መቻሉንም ገልጸዋል። ከዚህ በፊት ብሔራዊ ቡድን የሚመረጠው ፌዴሬሽኑ በሚያዘጋጀው አራት ዓይነት ውድድሮች ከ1-5 የሚወጡትን ተወዳዳሪዎች ሰብስቦ እርስ በርስ በማፎካከር እንደነበረ አስታውሰው፣ አሁን ግን ከበጀት እጥረት ምክንያት እነዚህን ውድድሮች በማካሄድ ብሔራዊ ቡድንኑን የመምረጥ እድሉ ጠባብ በመሆኑ በአንድ ውድድር ብሔራዊ ቡድን የሚወክሉ ስፖርተኞችን መምረጥ ግድ እንደሆነ ተናግረዋል። በዚህም መሠረት ጊዜያዊ ብሔራዊ ቡድን በመምረጥ አቅም የሚፈቅድ ከሆነ ቀሪ ውድድሮችን በማካሄድ ብሔራዊ ቡድኑን የሚቀላቀሉ ስፖርተኞች ሊኖሩ እንደሚችሉም ጠቁመዋል፡፡

በኢትዮጵያ ጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን ስር በየዓመቱ የሚደረጉ የተለያዩ ውድድሮች የሚገኙ ሲሆን ከነዚህም መካከል ፌዴሬሽኑ በጀት ይዞ የሚያወዳድራቸው እና የቴክኒክ ድጋፍ የሚያደርግላቸው ውድድሮች ናቸው። በፌዴሬሽኑ በጀት የሚካሄዱ ውድድሮች አንደኛና ሁለተኛ ዙር የክለቦች ሻምፒዮና፣ የኢትዮጵያ ሻምፒዮና እና ለሁሉም ክፍት የሆነ የግል የበላይነት የማስጠበቅ ውድድሮች ዋንኞቹ ናቸው፡፡

በውድድሩ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ኢትዮ ኤሌክትሪክ፣ ኦሮሚያ ፖሊስ፣ ኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ፣ ፒንግ ፖንግ፣ የኔነህ አዲስ፣ አሜድላ እና ወወክማ ተሳታፊ እንደ ነበሩ ተጠቁሟል።


## ክፍት የስራ መደብ ማስታወቂያ

አዲስ ፋና ጠቅላላ ሸቀጣ ሸቀጥና ሆቴሎች ንግድ አክስዮን ማህበር በሚከተለው የስራ መደብ ተወዳዳሪዎችን አወዳድሮ ቅጥር መፈፀም ይፈልጋል።

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ መጠሪያ | ብዛት | ተፈላጊ ችሎታ /መስፈርት/ | ደረጃ |
|---|---|---|---|---|
| 1. | የሆቴል ኃላፊ | 1 | ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በሆቴል ማኔጅመንት በቢዝነስ ማኔጅመነት ወይም በተመሳሳይ ትምህርት መስክ የመጀመሪያ ዲግሪና በሙያው የ4 ዓመት ተመሳሳይ የሥራ ልምድ፤<br>ወይም<br>ከታወቀ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በሆቴል ማኔጅመንት /በቢዝነስ ማኔጅመንት ወይም በተመሳሳይ ትምህርት መስክ የኮሌጅ ዲፕሎማና በሙያው የ6 ዓመት ተመሳሳይ የሥራ ልምድ ከዚህ ውስጥ 2 ዓመት በሆቴል ኃላፊነት የሠራ/ች<br>ወይም<br>ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት በሆቴል ማኔጅመንት በቢዝነስ ማኔጅመንት ወይም በተመሳሳይ የንግድ ስራ ትምህርት መስክ 10+2 የትምህርት ደረጃ ያጠናቀቀ/ችና በሙያው የ8 ዓመት ተመሳሳይ የሥራ ልምድ ያለው/ያላት<br>ወይም<br>በቀድሞ 12ኛ በአዲሱ 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀ/ች እና የ10 ዓመት አግባብ ያለው የሥራ ልምድ ያለው/ ያላት፤ | 12 |

* **ደመወዝ**.........................................በስምምነት

* **የሥራ ቦታ**........................................ጅማ ጊቤ ሆቴል

* **የመመዝገቢያ ቦታ**.................አዲስ አበባ ዋና መስሪያ ቤት የሰ/አስ/ስ/ማስተባበሪያ ቢሮ

**ማሳሰቢያ**:- አመልካቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የሥራ ቀናት የትምህርትና የሥራ ልምድ ማስረጃዎችን ኦርጅናልና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ ከማመልከቻ ጋር በመያዝ የሰራተኛ አስተዳደር ስልጠና ማስተባበሪያ በመምጣት መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**አድራሻ፡- ፒያሳ ራስ መኮንን ድልድይ አዲስ ፋና ጠቅላላ ሸቀጣ ሸቀጥና ሆቴሎች ንግድ አክሲዮን ማህበር (ኢትሆፍ)።**

**ስልክ ቁጥር፡ 0111567003**

## አዲስ ፋና ጠቅላላ ሸቀጣ ሸቀጥና ሆቴሎች ንግድ አክስዮን ማህበር